# የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በፊንላንድ መሰረተ እምነት እና መተዳደሪያ ደንብ

# Ethiopian Evangelical Church In Finland Statement Faith and Constitution.

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በፊንላንድ በ 1993 የመተዳደሪያ ድንብ አዘጋጅታ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በሔልሲንኪ በሚል ስም አገልግሎት ብትጀምርም ትተዳደር የነበረው በወንድማማች ፍቅር እና በመንፈስ አንድነት ላይ በተመሰረተ መግባባት እና ምክክር ነበር።

በ2000 አጋማሽ ላይ የሽማግሌዎች ጉባኤ ቤተክርስቲያኒቷ በፊንላንድ ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ፊት ለሚመሠረቱ አጥቢያ ቤተክርስቲያኖች እናት ትሆናለች በሚል እምነት የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በፊንላንድ ተብላ ተሰይማለች።

በ2011 የ1993 ቱ መተዳደሪያ ደንብ ተሻሽሎ በጠቅላላ ጉባኤ ጸድቆ የቤተክርስቲያኒቷ መተዳደሪያ ህግ ሆኖ እስከ 2016 አገልግሏል። በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ደንቦች ፣የእምነት አንቀጾች እና ተደራጊ ስርዓቶች በተደራረበ እና ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ ስለተቀመጡ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በሽማግሌዎች ጉባኤ በመወሰኑ ይህ በድጋሚ የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቷል። ይህ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በፊንላንድ መተዳደሪያ ደንብ ሁለት ክፍሎች ሲኖሩት፤ የመጀመሪያው ክፍል የቤተክርስቲያኒቱ መሰረተ እምነት ላይ ያተኮረ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የልዩ ልዩ አገልግሎት ክፍሎች መመሪያዎች እና ተፈጻሚ ስርአቶችን ያካትታል።

የመተዳደሪያ ደንቡ በቤተክርስቲያኒቷ ሊነሱ ለሚችሉ መንፍሳዊ እና አስተዳደራዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ያሚረዳ ነው። ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች ሁሉ የሚመለሱት በእውነትና በፍቅር በመነጋገር እና አብሮ በመጸለይ እንዲሁም እግዚአብሔርን ፈቃድ በመረዳት ነው።

በመጀመሪያ በዚ ሁሉ የረዳንን እግዚአብሔርን እጅግ እናመሰግናለን። በመቀጠልም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለዚህ መተዳደርያ ደንብ ተፅፎ እና ታርሞ መውጣት አስተዋፆ ያደረጋችሁትን ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር አምላክ ይባርካቹ ትላለች።

02. June, 2018

መክስዕተ አርዕስት(Table of content.)


አንቀጽ 1. ስም

አንቀጽ 2. ግንኙነት

አንቀጽ 3. መሰረተ እምነትዋ

3.1 እግዚአብሔር

3.2 እግዚአብሔር አብ

3.3 እግዚአብሔር ወልድ

3.4 እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

3.5 መጽሐፍ ቅዱስ

3.6 ድኅነት (Salivation)

3.7 ቤተክርስቲያን

3.8 ትንሣኤ ሙታን

3.9 ሰይጣን

3.10 የሰው አፈጣጠርና ውድቀት

3.11 የዘለዓለም ድኅነት(ዋስትና)

3.12 ቅድስና(መለየት)

3.13 ኅብረት(አንድነት)

3.14 የክርስቶስ ዳግም ምፅአት

3.15 ገነት

3.16 ሲዖል

3.17 መንግሥተ ሰማያት

3.18 የእሳት ባህር

አንቀጽ 4. ቅዱሳት ምሥጢራት

4.1 ቅዱስ ጥምቀት

4.2 የጌታ ራት

4.3 ቅዱስ ጋብቻ

አንቀጽ 5. የክርስትና ተደራጊ ሥርዓቶች

5.1 ልጆችን ለጌታ አደራ መስጠት

5.2 የቀብር ሥነሥርዓት

5.3 እግር የመተጣጠብ ሥርዓት

5.4 ለሕሙማን መጸለይ

አንቀጽ 6. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

6.1 ፈሪሀ እግዚአብሔር

6.2 ባለ አደራነት

6.3 አክብሮት

6.4 መታዘዝ

6.5 ሰላም

አንቀጽ 7. የቤተክርስቲያን አባልነት

7.1 የአባልነት መሥፈርት

7.2 የአባላት ግዴታ

7.3 የአባላት ሥነ ሥርዓታዊ ቅጣቶች

አንቀጽ 8. የሽምግልና አገልግሎት

8.1 የሽምግልና መስፈርት

8.2 የሽማግሌዎች ተግባር

አንቀጽ9. የአገልግሎት ስጦታዎች / የጥሪ አገልግሎት

9.1 መጋቢ

9.2 የመጋቢው ሃላፊነት እና ሥልጣን

9.3 ወንጌላዊ

አንቀጽ 10. የአገልግሎት ክፍል)

10.1 የአገልግሎት ክፍል ዝርዝር

10.2 የአገልግሎቶቹ ዝርዝር ተግባር

10.2 .1 የእህቶች አገልግሎት ክፍል

10.2 .2 የወጣቶች አገልግሎት ክፍል

10.2 .3 የሕፃናትና የታዳጊ ልጆች አገልግሎት ክፍል

10.2 .4 የፀሎት አገልግሎት ክፍል

10.2 .5 የጋብቻ እና የቤተሰብ ምክር አገልግሎት ክፍል

10.2 .6 የዲያቆናት አገልግሎት ክፍል

10.2 .7 የመዘምራን አገልግሎት ክፍል

10.2 .8 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልግሎት ክፍል

10.2 .9 የእርዳታና የመጽናናት አገልግሎት ክፍል

10.2 .10 የሚዲያ አገልግሎት ክፍል

10.2 .11 የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ክፍል

10.3 ዓላማ

10.4 ተጠሪነታቸው

10.5 አጠቃለይ መመሪያ

አንቀጽ 11. የቤተክርስቲያን ሥልጣንና ኃላፊነት

11.1 መስበክ

11.2 ሹመት

11.3 ማግለል

11.4 ፍትህ

11.5 ቸርነት

11.6 ምሥጢራት

አንቀጽ 12. ተጨማሪ መመሪያዎች

12.1 የጋብቻ መመሪያ

12.1.1 በቤተክርስቲያን የጋብቻ ሥርዓት የሚከናወንላቸው

12.1.2 በቤተክርስቲያን የጋብቻ ሥርዓት የማይከናወንላቸው

12.2 የእጮኝነት መመሪያ

12.3 ከአባልነት የሚያስገልሉ በተግሳጽ የሚታዩ መመሪያዎች

አንቀጽ 13. ተደራጊ ሥርዓተ ደንቦች

13.1 ልጆችን ለጌታ መስጠት

13.2 የውሃ ጥምቀት

13. 3 የጌታ ራት

13.4 ጋብቻ

13.5 ቅብዓተ ጸሎት

አንቀጽ 14. የሰራተኛ ደንብ

## አንቀጽ 1. ስም

በዚህ የቤተክርስቲያን መሰረተ እምነት እና መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተመሰረተችው ቤተክርስቲያን መታወቂያ ስም የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በፊንላንድ ይሆናል።

## አንቀጽ 2. ግንኙነት

ከመሰረታዊ ትምህርትዋ ጋር ከሚመሳሰሉት አብያተ ክርስቲያናት እና መንፈሳዊ አገልግሎት ከሚሰጡት ሁሉ ጋር ትተባበራለች።

## አንቀጽ 3. መሰረተ እምነትዋ

### 3.1 እግዚአብሔር

በሰማይና በምድር የሚገኙትን ፍጥረታት ሁሉ በፈጠረ፣ ሁሉን ቻይ፣ታላቅ፣ ዘለዓለማዊ ፣ ፍጹም የማይለወጥ ፣ራሱን በሦስት አካል በአብ ፣በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ በሚገልጥ በአንድ አምላክ ታምናለች።

ዘፍጥረት 1፡26፤ ዘዳግም 6፡4-5፤ መዝሙር 89(90)፡2፤ መዝሙር 138(139)7-21፤ መዝሙር 146(147)፡5 ፤ትንቢተ ኢሳያስ 40፡28፤ ትንቢተ ሚልኪያስ 3፡6፤ የዮሐንስ ወንጌል 17፡11

### 3.2 እግዚአብሔር አብ

እግዚአብሔር አብ በፍቅሩ፣ በምህረቱ እና በቃሉ በኩል ለሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ በገባው ቃል ኪዳን መሰረት የሰጠውን የተስፋ ቃል በመጠበቅ በአምሳሉ ለፈጠረው ሰው በልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የዘለዓለም ድኅነትን እንዳዘጋጀ እርሱንም እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው አምነው ለተቀበሉ እና ኃጢያታቸውን ለሚናዘዙ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅነትን ሥልጣን እንደሚሰጣቸው ታምናለች ።

ዘፍጥረት 17፡1-2፤ ዘፍጥረት 22፡16-18፤ ዘጸአት 3፡15፣ ዘጸአት 6፡2-5፤ የዮሐንስ ወንጌል 1፡29፤ የዮሐንስ ወንጌል 1፡12፤ የዮሐንስ ወንጌል 3፡16፤ ኤፌሶን 4፡6

### 3.3 እግዚአብሔር ወልድ

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ ዘላለማዊ ልጅ መሆኑን ከመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ ከድንግል ማሪያም መወለዱን ፤ ፍጹም ሰው እና ፍጹም አምላክ ሆኖ መዋሃዱን፣ ኃጢአት ያለሰራ የኃጢአተኞች ምትክ ሆኖ መላኩን ፣በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን በማፍሰስ ለኃጢአተኞች ራሱን ቤዛ አድርጎ ሰውን ዋጅቶ ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ ከሞት

ተነሥቶ በክብር ማረጉን፣ ለሰው ልጅ ሁሉ ሊማልድ ዘወትር በአባቱ ቀኝ በሕይወት መኖሩን፣ የቤተክርስቲያን መስራች እና ራስ መሆኑን እና ለፍርድም ዳግመኛ ተመልሶ እንደሚመጣ ታምናለች።

ዘፍጥረት 3፡15፤ የማቴዎስ ወንጌል 1፡20-23፤ የዮሐንስ ወንጌል 1፡1-14፤ የሉቃስ ወንጌል 1፡35፤ የሐዋሪያት ሥራ 17፡31፤ ዕብራዊያን 9፡13፡4

### 3.4 እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ምላተ አካል እንዳለውና መለኮት መሆኑን፣ ዓለምን ስለ ኃጠአት ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ እንደሚወቅስ በምዕመናን ወስጥ አድሮ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው ፣ እንደሚያጽናናቸው፣የቅድስና ኑሮ ለመኖር እንደሚያስችላቸው፣ ለአገልግሎትም ኃይልን እንዲሁም ለአካሉ ብርታት የፀጋ ስጦታዎችን እንደሚሰጣቸው ታምናለች።

ዘፍጥረት 1፡2፤ የዮሐንስ ወንጌል 16፡7-8፤ የሐዋሪያት ሥራ 1፡8፤ ሮሜ 8፡1-4፤ ገላቲያ 4፡6፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1፡21

### 3.5 መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ እና ሐዲስ ኪዳን በመባል የተሰየሙ በውሥጣቸው በቁጥር ስልሳ ስድስት (66) መጽሐፍት በመላው በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ቅዱሳን ሰዎች እንደፃፉት በማመን ሰው ሁሉ ሊታመንበት የሚገባ የቤተክርስቲያን እምነትና እንዲሁም የእግዚአብሔር ሥርዓት ምንጭ ደግሞም መለኪያ የሆነ እንደሆነ፤ እንደዚሁም ኃይልና ሥልጣን ያለው ከስህተት የራቀ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ታምናለች።

ዘሌዋዊያን 8፡35-36፤ 2ኛ ሳሙኤል 23፡2፤ መዝሙር 12፡6፤ የማቴዎስ ወንጌል 24፡35፤ የዮሐንስ ወንጌል 17፡17፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 2፡3፤ ዕብራውያን 4፡12፤ 2ኛ ጢሞቴዋስ 3፡15-17፤ ያዕቆብ 1፡25፤ የዮሐንስ ራእይ 22፡8-9

### 3.6 ድኅነት

ስለ ሰው ሁሉ ኃጢአት በመስቀል ላይ በመሞት ራሱን ቤዛ አድርጎ በሰጠው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፀጋ ብቻ እንደሚድን ታምናለች። እንዲሁም በአምሳሉ ሁሉ የተፈጠረው ሰው በኃጢያቱ ተጸጽቶ ንስሃ በመግባት በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ተወልዶ የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን እንደሚሰጠው እንዲሁም ደግሞ በክርስቶስም መንፈሳዊ ባረኮትን በመቀበል የዘለዓለም ሕይወትንም እንደሚያገኝ ታምናለች።

ትንቢተ ኢሳያስ 53፡4-12፤ የዮሐንስ ወንጌል 1፡12-13፤ የሐዋሪያት ሥራ 13፡38-39፤ ሮሜ 3፡20-26፤ ኤፌሶን 2፡8-9

## 3.7 ቤተክርስቲያን

ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን መሰረት እና መስራች እንዲሁም ራስና መሪ እንደሆነ ታምናለች። ቤተክርስቲያን ክርስቶስን በማመን ንስሐ ገብተው ዳግመኛ የተወለዱና መንፈስ ቅዱስም አንድ አካል ያደረጋቸው ምዕመናን ሁሉ ያሉባት የክርስቶስ አካል መሆንዋን በማመን ለክርስቶስም ቃል በፍጹም መታዘዝ እንዳለባቸው ታምናለች።

የማቴዎስ ወንጌል 16፡18፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 3፡11፤ ኤፌሶን 2፡20-22፤ ኤፌሶን 5፡23፤ ዕብራውያን 3፡1፤ የሐዋሪያት ሥራ 16፡31፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡12-27፤ ገላቲያ 3፡26፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡9-10

## 3.8 ትንሣኤ ሙታን

ኢየሱስ ክርስቶስ የማይሞትና የማይበሰብስ አካል ለብሶ ከሙታን መካከል እንደተነሳ እንዲሁም ጻድቃንና ኃጢአንን በማይሞትና በማይበሰብስ አካል ከሙታን ተነስተው ጻድቃን ወደ ዘለዓለም ደስታ ፣ ኃጢአን ደግሞ ወደ ዘለዓለም ስቃይ እንደሚሄዱ ታምናለች።

ትንቢተ ዳንኤል 12፡2፤ የዮሐንስ ወንጌል 5፡28-29፤ የዮሐንስ ወንጌል 20፡24-29፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡20-23፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡42-44፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡51-54

## 3.9 ሰይጣን

ሰይጣን የሆነው አስቀድሞ ግን ኪሩብ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ጥበበኛ ደግሞም ውብ አድርጎት በመፍጠር ፍጹምና ፈጣሪውን የሚያገለግል ታላቅ መልአክ እንደነበር ፤ ሆኖም እንደ እግዚአብሔር ታላቅ ለመሆን በነበረው ምኞት ሌሎችንም መላእክት እንዳሳሳተና እንደ ወደቀ በእባብ ተመስሎ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምጹ ያታለለ በባህሪው የረከሰ፣ሐሰተኛ፣ የኃጢያትና የጥፋት ሁሉ ምንጭ ፣ የእግዚአብሔር እና የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት ፣ የጨለማው ዓለም ገዥ እንደሆነ በመጨረሻም ከተከታዮቹ ጋር ወደ እሳት ባህር እንደሚጣል ታምናለች።

ዘፍጥረት 3፡1-6፤ ትንቢተ ኢሳይያስ 14፡12-15፤ ትንቢተ ሕዝቅኤል 28፡12-19፤ የማቴዎስ ወንጌል 25፡41፤ የማርቆስ ወንጌል 1፡27፤ የዮሐንስ ወንጌል 8፡44፤ ኤፌሶን 6፡12፤ 1ኛ ዮሐንስ መልዕክት 5፡19፤ 1ኛ ጴጥሮስ 5፡8፤ የዮሐንስ ራእይ 20፡10

## 3.10 የሰው አፈጣጠርና ውድቀት

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን በራሱ መልክ እና አምሳል መልካም አድርጎ ፈጥሮት ሳለ ይህም ሰው በሰይጣን ተታሎ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣሱ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሙት በመሆኑ ፣ ኃጢያተኛ በመሆኑ፣ ከሥጋዊ ሞት እና ከሰይጣን ሥልጣን በታች በመሆኑ ከዚህም ውድቀት ራሱን በራሱ ለማዳን የማይችል ፍጡር እንደሆነ ታምናለች።

ዘፍጥረት 1፡26-27፤ ዘፍጥረት 2፡17፤ ዘፍጥረት 16፡17፤ ዘፍጥረት 3፤1-22፤ የዮሐንስ ወንጌል 8፡44፤ ሮሜ 5፡6፤ ሮሜ 5፡8፤ ኤፌሶን 2፡1-3፤ ኤፌሶን 2፡12

## 3.11 የዘለዓለም ድኅነት(ዋስትና)

በኃጢአታቸው ተፀፅተው በንስሃ በጌታ ያመኑ የእርሱ ምዕመናን (አማኒያን) ባመኑበት ወቅት ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገራቸውን ለማወቅ እንደሚችሉ፣ እግዚአብሔር ከመውደቅ ሊጠብቃቸው እንደሚችል በቅዱስ ቃሉ የተገፈ እንደሆነ፤ ሆኖም በእርሱ ፀጋ ለማደግና ከጌታም ላለመለየት ድኅነታቸውን ለመጠበቅ በእምነት የመታዘዝ ሃላፊነት እንዳለባቸው ታምናለች።

የዮሐንስ ወንጌል 5፡14፤ ሮሜ 8፡16፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡1-3፤ 1ኛ ጴጥሮስ 3-51፤ ዕብራውያን 3፡12-19፤ 1ኛ ዮሐንስ 5፡13፤ ይሁዳ፡24-25

## 3.12 ቅድስና(መለየት)

ማንኛውም በጌታ የዳነ ሰው ከዳነበት ቀን ጀምሮ ከዓለማዊነት እንዲሁም በዓለም ውስጥ ካሉት ከንቱ ነገሮች ተለይቶ ለእግዚአብሔር ክብር በኢየሱስ ክርስቶስ የጽድቅ ኑሮ መኖር እንደሚገባው ታምናለች።

የዮሐንስ ወንጌል 17፡15፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 6፤14-18፤ቲቶ 2፡11-14

## 3.13 ኅብረት(አንድነት)

በክርስቶስ አዳኝነት ያመኑ ሁሉ በእርሱ አንድ ኣካል በመሆናቸው በመንፈስ አንድነት እንዳላቸው ታምናለች።

ሮሜ 12፡15፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13-26፤ ኤፊሶን 4፡1-7

## 3.14 የክርስቶስ ዳግም ምፅአት

የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት የአማኒያን ሁሉ ተስፋ መሆኑንና በምፅዓቱ ጊዜ በሕይወት ያሉና ከሙታን የሚነሱ ምዕመናን ሁሉ ጌታን በአየር እንደሚቀበሉት ከዚያም በኋላ ለዘለዓለም በደስታ ከእርሱ ጋር እንደሚኖሩ ታምናለች።

የማቴዎስ ወንጌል 24፡24፣25፣30፣31፣44፤ የማቴዎስ ወንጌል 25፡31፤ የዮሐንስ ወንጌል14፡3፤ የሐዋሪያት ሥራ 1፡11፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13-18፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡28

## 3.15 ገነት

ገነት በሞት እና በትንሣኤ መካከል ባለው ጊዜ ጻድቃን ከክርስቶስ ጋር በሰማይ በደስታ የሚኖሩባት ቦታ እንደሆነች ታምናለች።

የሉቃስ ወንጌል 23፡43፤ ፊልጲስዩስ 1፡21-23

## 3.16 ሲዖል

በሞትና በትንሣኤ መካከል ባለው በክርስቶስ አዳኝነት ያላመኑ ሁሉ በስቃይ የሚኖሩባት ቦታ መሆኑን ታምናለች

የሉቃስ ወንጌል 19፡19-31፤ 2ኛ ጴጥሮስ 2፡10

## 3.17 መንግሥተ ሰማያት

መንግሥተ ሰማያት በጌታ ያመኑ አማኒያን ለዘለዓለም በልዩ ደስታ የሚኖሩባት ዘለዓለማዊ ሥፍራ መሆኑን ታምናለች። የማቴዎስ ወንጌል 25፡34፤ የዮሐንስ ራእይ 14፡13፤ የዮሐንስ ራእይ 21፡1-7፤ የዮሐንስ ራእይ 22፡1-5

## 3.18 የእሳት ባህር

የእሳት ባሕር አስቀድሞ ለሰይጣን ባለመታዘዙ ምክንያት የተዘጋጀለት የዘለዓለም መቀጫ ቦታ ሲሆን የእርሱንም ፈቃድ በማድረግ ለተከተሉ ሁሉ የተዘጋጀላቸው ዘለዓለማዊ መቀጫ ቦታ መሆኑን ታምናለች።

የማቴዎስ ወንጌል 25፡41፣46፤ የዮሐንስ ራእይ 14፡8-11፤ የዮሐንስ ራእይ 20፡10-15፤ የዮሐንስ ራእይ 21፡8

# አንቀጽ 4. ቅዱሳት ምሥጢራት

ቅዱሳት ምሥጢራት የሚባሉት በሚታይ እንዲሁም በሚጨበጥ መንገድ መንፈሳዊ ምሥጢርን የሚገልጡ ፤ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ የፈጸማቸውና እንድንፈጽማቸውም ያዘዘን ፣ በጌታ ኢየሱስ ውስጥ ትርጉምና መንፈሳዊ ምሥጢራትን ያዘሉና ብናደርጋቸው በረከትን የሚያስገኙ መሆናቸውን ታስተምራለች ደግሞም በማመን ተግባራዊ ታደርጋለች።

1 ጢሞቴዎስ 3፡8-10፣16

## 4.1 የውሃ ጥምቀት

ሰው ንስሃ ገብቶ ኢየሱስን በእምነት አዳኝና ጌታ አድርጎ በመቀበል ከዳነ በኋላ በአብ ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ውስጥ በማጥለቅ የሚከናወነውን ጥምቀት ቃሉን መሰረት በማድረግ ታከናውናለች ።

የማቴዎስ ወንጌል 28፡19-20፤ የሐዋሪያት ሥራ 2፡37-41፤ የሐዋሪያት ሥራ16፡30-34፤ ሮሜ 6፡1-8፤ ቆላስይስ 2፡12

## 4.2 የጌታ ራት

የጌታ ራት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአት ሥጋው መቆረሱንና ደሙም ስለ ሰው ሁሉ ኃጢአት መፍሰሱን የሚያመላክት ነው ፣ይህም በኅብስትና በጽዋ ምሳሌ ሆኖ የሚከናወን የጌታን ሞት መታሰቢያ ነው። ይህንን ራት መሳተፍ የሚገባቸውም ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉ፣ የውኃ ጥምቀት የወሰዱ እና በቅድስና የተመላለሱ ምዕመናን ብቻ እንደሆኑ ታምናለች።

የማቴዎስ 26፡26-28፤ የሐዋሪያት ሥራ 2፡42፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡16-17፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡17-34

### 4.3 ቅዱስ ጋብቻ

ጋብቻ በእግዚአብሔር ቃል መሰረት በአንድ ወንድ እና በአንዲት ሴት መካካል ብቻ የሚፈጸም እግዚአብሔር የመሰረተው ደግሞም የቀደሰው የሁለት ተቃራኒ ፆታ አማኒያን አንድነት ነው።ይህን ኪዳን ሊሽረው የሚችል ሞት ብቻ ሲሆን ቤተክርስቲያን ይህንን ቅዱስ ሥርዓት ልትንከባከበው ደግሞም ልትጠብቀው የሚገባት ቅዱስ ሥርዓት መሆኑን ታምናለች።

ዘፍጥረት 2፡18-25፤ የማቴዎስ ወንጌል 19፡3-9፤ ሮሜ 7፡1-13፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡10-16፣39፤ ኤፌሶን 5፡23-33፤ ዕብራዊያን 13፡14

## አንቀጽ 5. የክርስትና ተደራጊ ሥርዓቶች

በመጽሐፍ ቅዱስ በሁለቱም ኪዳኖች ውስጥ ማድረግ የሚገቡንን የተለያዩ ሥርዓቶችን እንድናደርግ ያዝዘናል እነዚህም የክርስትና ሥርዓቶች ተብለው የሚጠሩ ሲሆን በቤተክርስቲያን ትዕዛዝ የሚደረጉ መንፈሳዊ ሥርዓቶች ናቸው።

### 5.1 ልጆችን ለጌታ አደራ መስጠት

ልጆችን ለጌታ አደራ መስጠት በብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር ለሕዝበ እሥራኤል ተሰጥቶ በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ሕይወቱ ላይ የተፈጸመ እርሱም በአገልግሎቱ ጊዜ በተግባር ሲተገብረው የነበረና ቤተክርስቲያንም ከአማኝ ወላጆች ለተወለዱ ሕጻናት የምታከናውነው ሥርዓት እንደሆነና ይህም ሥርዓት ሕጻናት ከእግዚአብሔር ባርኮት እና ጥበቃ እንዲያገኙ ለጌታ አሳልፈን የምንሰጥበትና ወላጆችም እግዚአብሔርን በማመስገን በጌታ መንገድ እና ሥርዓት ሕጻናት ልጆቻቸውን ለማሳደግ ቃል የሚገቡበት ሥርዓት መሆኑን ታምናለች።

ዘፍጥረት 10፡17-19፤ ዘሌዋውያን 12፡1-8፤ የማርቆስ ወንጌል 10፡13-16፤ የሉቃስ ወንጌል 2፡22-28

### 5.2 የቀብር ሥነሥርዓት

አንድ አማኝ በሥጋው ሲሞት ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሥርዕትን ታደረጋለች። ይህም በሀዘኑ የተጎዱትን ቤተሰቦቹን በጌታ ቃል በማበረታታት እንዲሁም የቀብሩ ሥነስርዓት በሚደረግበት ጊዜ ለአማኔያን መጽናናት ብቻ ሳይሆን ላላመኑ ሁሉ ከሞት በኋላ ስላሉት እውነቶች በመስበክ አማኞችን በማጽናናት ከእምነት ውጪ ያሉትን ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመጡ ቃሉን በማሰማት ሃላፊነታችንን በጊዜው የምንወጣበት እንደሆነ ታምናለች።

መክብብ 7፡2፤ የሐዋሪያት ሥራ 8፡2፤ የማቴዎስ ወንጌል 27፡57-61፤ ሮሜ 12፡15

### 5.3 እግር የመተጣጠብ ሥርዓት

የእግር መተጣጠብ ሥርዓት ምዕመናን የጌታ ራት ሥርዓትን ከተካፈሉ በኋላ ሊፈጽሙት የሚገባ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በምድር በነበረበት ጊዜ የፈፀመው እንዲሁም እርሱ ወደዚህ ዓለም እስከሚመጣ ድረስ ቤተክርስቲያን እንድታከናውነው ጌታ የደነገገው ሥርዓት መሆኑን ታምናለች።

የዮሐንስ ወንጌል 13፡1-17

### 5.4 ለሕሙማን መጸለይ

ሕሙማን በጸሎት ሊፈወሱ እንደሚችሉ በማመን በቤተክርስቲያን ውስጥ ሃላፊነት የተሠጣቸው ቅብዓተ ዘይት ቀብተው የእምነት ጸሎት መደረግ እንዳለበት ታምናለች። እንዲሁም በማርቆስ ወንጌል 16:17-20 ላይ እንደተጻፈ የሚያምኑ ሁሉ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ ብላ ታምናለች።

ዕብራዊያን 6፡1-2፤ ያዕቆብ 5፡14-16፤ የማርቆስ ወንጌል 16:17-20

## እንቀጽ 6. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድረገው የተቀበሉ አማኒያን ሁሉ በምድራዊ ሕይወታቸው በእምነታቸው እና በሌላው ኖሮአቸው ሁሉ ምሳሌ መሆን እንደሚገባቸው ቃሉ በዋናነት የሚያዘን ሲሆን ይህን በማድረግ ሌሎች ወደ ጌታ እንዲመጡ ምክንያት ልንሆናቸው እንደምንችል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በምድር አገልግሎቱ አበክሮ የተናገረው ደግሞም ያስተማረው ዋና ትምህርት እንደሆነ ስለዚህ ማንኛውም አማኝ ይህንኑ እውነት በማድረግ ምሳሌ መሆን እንዳለበት ታምናለች።

የማቴዎስ ወንጌል 5፡1-16

### 6.1 ፈሪሀ እግዚአብሔር

ማንኛውም አማኝ ከሁሉ በላይ በቅድሚያ እግዚአብሔርን መፍራት፣ማፍቀር እና በሁሉ በመታዘዝ በግል እና በጋራ ሕይወታው እርሱን ማክበር እንደሚገባ ቤተ ክርስቲያን ታምናለች።

መጽሐፈ ምሳሌ 1፡7፤ የማቴዎስ 22፡37፤ የሐዋሪያት ሥራ 4፡18-20፤ የሐዋሪያት ሥራ 5፡29

### 6.2 ባለ አደራነት

ማንኛውም አማኝ ለዓለም ክብርና ጥቅም ሳይሸነፍ በኑሮውና ከእግዚአብሔር በተሰጠው ማንኛውም ነገር ባለ አደራነቱን ሳይዘነጋ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም እንደሚገባው ቤተ ክርስቲያን ታምናለች።

መጽሐፈ ምሳሌ 3፡9-10፤ ትንቢተ ሚልኪያስ 3፡7-12፤ የሉቃስ ወንጌል 12፡35-48፤ ሮሜ 12፡1-2፤

1ኛ ዮሐንስ 2፡1-6፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡15-17

### 6.3 አክብሮት

ምእመናን ቤተክርስቲያንን እና የቤተክርስቲያን መሪዎችን (አገልጋዮችን) በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ሊያከብሯቸው ሊወዳቸውና ሊታዘዟቸው እንደሚገባ ቤተክርስቲያን ታምናለች።

1ኛ ተሰሎንቄ 5፡12-13፤ ዕብራዊያን 13፡17

### 6.4 መታዘዝ

እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት ለሀገርና ለሀገር መሪዎች በታማኝነት፣ በቅንነት፣ በመታዘዝ ማክበር እና የሚፈለግብንን ግብር መክፈል እንዲሁም ለአገር መሪዎችም መጸለይ እንደሚገባቸው ታምናለች ቃሉንም መሰረት በማድረግ ደግሞ ታስተምራለች።

ሮሜ 13፡1-7፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-4

### 6.5 ሰላም

አማኒያን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላምና በፍቅር መኖር እንዳለባቸው ታምናለች።

ዘሌዋውያን 19፡17-18፤ ሮሜ 12፡14-21

## አንቀጽ 7. የቤተክርስቲያን አባልነት

በቅዱስ ቃሉ በዋናነት ከተፃፉልን መልዕክቶች መካከል አንዱ ስለ ቤተክርስቲያን ማንነት ማወቅ ነው፤በምድር ያለችው ቤተክርስቲያን የክርስቶስ መሆኑዋን በመረዳት ቀዳሚ ከሆኑት ተጨባጭ ማሳያዎች መካከል አንዱ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ተቋም መሆኑዋ ነው፤ ስለዚህ በክርስቶስ ያመኑ በምድር ላይ ባለችው አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ በመሆን ወንጌልን መሰረት በማድረግ የምታገለግለው ይህች ቤተክርስቲያን በውስጡዋ ያሉት ደግሞም ወደፊት ጌታን በእምነት በመቀበል ለሚመጡት ሁሉ የአካሉ ብልቶች የቤተክርስቲያን አባላት ተብለው ይጠራሉ።

### 7.1 የአባልነት መሥፈርት

ጌታ አየሱስ ክርሰቶስን በማመን እርሱንም እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉ፣ ደግሞም የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በፊንላንድ ያላትን መተዳደሪያ ደንብ በመቀበል በመቀጠልም የውሃ ጥምቀት የወሰዱ ሁሉ የቤተክርሰቲያኒቱ አባል ይሆናሉ፤ በተጨማሪ ከሌላ እህት ቤተክርስቲያን ማለትም በመሰረተ እምነት ከሚመሳሰሉት አብያተክርስቲያነት በተለያዩ ጉዳዮች ተዘዋውረው የመጡ ሁሉ ከነበሩበት ቤተክርስቲያን የመሸኛ ደብዳቤ ያላቸው ሁሉ አባል ይሆናል፤ ሆኖም ተባባሪ አባል ለመሆን ሲጠይቁ ብቻ በተባባሪ አባልነት ይቆጠራሉ ሆኖም ግለሰቦቹ እስካልፈለጉ ድረስ አብረው እንዳያመልኩ ምንም ነገር አይከለክላቸውም፤ተባባሪ አባል በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ በሽምግልና ፣ በድቁና ውስጥ ሊመረጡ ደግሞም የመምረጥም መብት ሊኖራቸውም አይችልም። የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ቤተክርስቲያን ለአባላት በምትሰጠውን አገልግሎት የመገልገል መብት አላቸው።

### 7.2 የአባላት ግዴታ

1. በአንቀጽ ሦስት(3) ላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ የተቀበሉ ሊሆኑ ይገባቸዋል።
2. የእግዚአብሔርን ቃል መሰረት በማድረግ ለቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ሙሉ በሙሉ የሚታዘዙ መሆን አለባቸው።
3. በቤተክርስቲያኒቱ የአምልኮ እና የተለያዩ ስብሰባዎች ላይ መገኘት ይኖርባቸዋል።
4. በጊዜአቸውና በገንዘባቸው ታማኞች ሊሆኑ ይገባቸዋል።

5. በያሉበት ሁሉ የክርስቶስ እውነተኛ ምስክሮች ሊሆኑ ይገባቸዋል።

6. እግዚአብሄር በውስጣቸው ባስቀመጠው ጸጋ ቤተክርስቲያንን እና ቅዱሳንን የማገልገል ሃላፊነት አለባቸው።

## 7.3 የአባላት ሥነ ሥርዓታዊ ቅጣቶች

መንፈሳዊ ሕይወት የፍቅር እንደዚሁም እንደ እግዚአብሔር ቃል የምንመራበት የግል እና የጋራ ሕይወትም ነው፤ ከዚህ ሕይወት ጎድለው የተገኙ የእግዚአብሔርን ቃል መሰረት በማድረግ በየደረጃው ምክርን በመስጠት ሊመለሱ ፈቃዳኛ ያልሆኑትን የተለያዩ ቅጣቶች ይወሰንባቸዋል፤ እንደ ችግሩም ክብደት ከአግልግሎት ብቻ ሳይሆን ከቤተክርስቲያንም አባልነት ሊወገዱም ይችላሉ።

1. በእርስ በእርስ ግንኙነት ባለ መበዳደል የይቅርታ ሕይወት የሌላቸው።
2. እንደ እግዚአብሔር ቃል የማይኖሩ ለሌላው ማሰናከያ የሚሆኑ።
3. የሚያሰክር መጠጥ የሚጠጡ እንደዚሁም ሰውነታቸውን ሊጎዳ ደግሞም ሊያደነዝዝ የሚችል የተለያዩ አደንዛዥ ዕፅ ነገሮችን የሚጠቀሙ እንዲህ የመሳሰሉትን የሚነግዱ ሁሉ።
4. የሚያመንዝሩ ዘማዊያን።
5. የእግዚአብሔር ቃል የማይደግፈውን የተሳሳተ አስተምህሮ የሚያስፋፉ ።

ከላይ የተዘረዘሩትና እና ተጨማሪ የሆኑ ጥፋትን ያደረጉ ጥፋታቸውን በመቀበል በትክክለኛ ለውጥ የሚስተካካሉ ከሆነ ወደ አገልግሎታቸው ሙሉ በሙሉ ይመለሳሉ ሆኖም ምንም ዓይነት ለውጥ ካላመጡ በጉባዔ በማስታወቅ ሙሉ በሙሉ ከአባልነት ይሰረዛሉ።

ዘሌዋውያን 19፡17፤ ምሳሌ 20፡2፤ ምሳሌ 23፡20፤ የማቴዎስ ወንጌል 5፡23-24፤ የማቴዎስ ወንጌል 18፡15-18 ፤1ኛ ቆሮንቶስ 6፡1-7፤ ያዕቆብ 4፡11፤ ቲቶ 3፡10-11፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡14፤ 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡14-15፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡20፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡14-20፤ ኤፌሶን 5፡18፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡13፤ 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡6

# አንቀጽ 8. የሽምግልና አገልግሎት

ይህ አገልግሎት በመጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጥ አገልግሎት እንደሆነ በቅዱስ ቃሉ ላይ ተገልጾ እንመለከተዋለን። ሽማግሌዎች ከአጥቢያ ምዕመናን ውስጥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የተመሰከረላቸው የአጥቢያይቱ አባላት በድምፅ ብልጫ ይመረጣሉ። እነዚህ ሽማግሌዎች ተጠሪነታቸው ለጠቅላላ ጉባኤ/ማዕበረ ምዕመናን ይሆናል።

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡1-7፤ ቲቶ 1፡5-11፤ 1ኛ ጴጥሮስ 5፡1-4፤ ዘጸአት 24፡1፤ ዘኁልቅ 11:16

## 8.1 የሽምግልና መስፈርት

1. በመንፈሳዊ ሕይወቱ ፍሬ ያለው እንዲሁ ከማኅበር ምዕመናኑ የተመሰከረለት በግሉም ስለ ድነቱ የተረዳ መሆን ይገባዋል። እንዲሁም በውጭ ባሉት ዘንድ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንደ እግዚአብሔር ቃል የተመሰከረለት በቤተክርስቲያን አገልግሎቶች የሚካፈል በኑሮውም ምሳሌነት ያለው ሊሆን ይገባል።
2. የቤተክርስቲያኒቱን መተዳደሪያ ደንብ በሙሉ የተቀበለ መሆን ይገባዋል።
3. የአንዲት ሚስት ባል የሆነ መሆን አለበት። በእርሱ ቁጥጥር ስር ያሉ ልጆች ዕድሜያቸው ከ 18 በታች የሆኑ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የተመሰከረላቸው ሊሆኑ ይገባል ።
4. ለምርጫ ወይም ለእጩነት የሚጠቆመው አማኝ ቢያንስ ለአንድ አመት የቤተክርስቲያኒቷ አባል የሆነ እና በአገልግሎቱ ፍሬ የታየበት ሊሆን ይገባል።
5. በአጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ሞያተኛ ተቀጣሪ ሰራተኛ ያልሆነ መሆን አለበት።

## 8.2 የሽማግሌዎች ተግባርና ሥልጣን

1. ተጠሪነታቸው ለማህበረ ምእመናኑ ይሆናል።
2. የቤተክርስቲያንን አጠቃላይ ሁኔታ የቆጣጠራሉ ፣ በወር አንድ ግዜ ይሰበሰባሉ በዚህን ግዜ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው አስተዳደራዊ እና መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን ይሰጣሉ።
3. ከጥሪ አገልጋዮች እና ከሞያተኛ ሰራተኞች ጋር የቅጥር ውል ይፈጽማሉ አፈጻጸሙን ይከታተላሉ።
4. የቤተክርስቲያንን ወጪና ገቢ ገንዘብ እንዲሁም ለተለያዩ መንፈሳዊ እና ተዘማጅነት ላላቸው እንቅስቃሴዎች የጸደቀውን በጀት ሁሉ ይቆጣጠራሉ።
5. እንደተሰጣቸው ጸጋ የተለያዩ ትምህርቶችን ያስተምራሉ።
6. መጋቢውን በመርዳት የጌታ ራት፣የጥምቀት እና ልጆችን በመስጠት ሥርዓት ላይ በጋራ ያከናውናሉ።
7. የቤተክርስቲያኒቱ የጥሪ አገልጋዮችን አገልግሎት ይገመግማሉ።
8. አባላትን ይጎበኛሉ ፣ በእግዚአብሔር ቃል ይመክራሉ ረዳት የሌላቸውን ባልቴቶች እንዲረዱ ያደርጋሉ።
9. የሽምግልና አገልግሎታቸውን በተመለከተ በአመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ሪፓርት ያቀርባሉ።
10. በማንኛውም አገልግሎት ውስጥ አባል ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ ሆኖም የሽምግልና መብታቸውን በማንኛውም ውሳኔ ላይ አይጠቀሙበትም።
11. በጥሪ አገልጋዮች ላይ ምዕመናን ቅሬታ ቢኖራቸው ፥ ቅሬታቸውን የመስማት እና ለአገልጋዮች የሚቀርቡ ሂሶችን አጣርቶ ፥ ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ በትህትና እና በኀነት በተሞላ መልክ ለአገልጋዮች የማቅረብ አስቀድሞም ስለቀረበው ቅሬታ የመወያየት አስፈላጊውን ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አላቸው።

12. በማንኛውም መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ከመጋቢው ጋር የመንፈስና የልብ አንድነት ሲኖር ውሳኔ ይሰጣሉ፣ መጋቢውና ሽማግሌዎች ባልተስማሙበት ጉዳይ ላይ የሽማግሌዎች ጉባዔ በ2/3ኛ ድምጽ ከደገፉት የሽማግሌዎች ውሳኔ ይጸናል።

## 8.3 ሥርኣተ ምርጫ

1. ሽማግሌዎች እንደ እግዚአብሄር ቃል መርምረው እጩዎች ያቀርባሉ። መዕመናን ከቀረበላቸው እጩዎች በሚስጥር የምርጫ ሳጥን ሽማግሌዎችን ይመርጣሉ።
2. ልዩ ችግር ካልተፈጠረ በስተቀር በየዓመቱ በየካቲት ወር አጋማሽ ላይ የሚካሄድ ይሆናል።
3. የሽማግሌዎች ምርጫ የሚደረገው ሽማግሌዎች እና መጋቢው ከአስመራጭ ኮሜቴ ጋር በመሆን የሚደረግ ይሆናል በምርጫ የሚሳተፉት የቤተክርስቲያኒቱ አባል የሆኑ ብቻ ይሆናሉ።
4. የአባሉቱ ቁጥር ሌላ ለውጥ እስካልመጣ ድረስ ቁጥሩ እንደ ሁኔታው የተለያየ ቁጥር ሊኖራቸው ይችላል ሆኖም ድምፅ ለመስጠት አመቺ እንዲሆን በጎዶሎ ቁጥር ሆኖ የኣባላቱ ቁጥር ግን ከሦስት(3) በመጀመር እንደ እድገታችን ይወሰናል።
5. የሽማግሌ አገልግሎት ዘመን ለሁለት ዓመታት ይሆናል እንደገና የመመረጥ መብት ሲኖረው ከሁለት ተከታታይ ምርጫ በኋላ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ለምርጫ አይቀርቡም ሆኖም በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሊቀጥል ይችላል። አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ግን ለአንድ ዓመት ከሽምግልና አገልግሎት መውጣት ይኖርበታል።
6. ለሥራ አካሄድ እንዲያመች ሽማግሌዎች በሙሉ በአንድ ጊዜ ከሽማግሌነት አይገለሉም።እንዲህ ዓይነት ችግር ቢፈጠር ከመጋቢው ጋር በማስተባበር መፍትሔ የሚገኝበትን ሀሳብ በመመካከር ለጠቅላላ ጉባዔው ሁኔታውን ያቀርባሉ።
7. በሽምግልና አገልግሎት ውስጥ እያገለገሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል ጎልቶ የሚታይ አስነቃፊ ነገር ቢኖር በመሪዎች ጉባኤ ውሳኔ አገልግሎቱን ለጊዚው ሊያስቆሙት ይችላሉ። ክስተቱ ከበድ ያለ ጉዳይ ከሆነ ከጠቅላላ ጉባዔው ጋር በመመካከር ቃሉን ማዕከል በማድረግ ጊዜያው እና ዘለቄታዊ መፍትሔ ይበጅለታል።
8. ሽማግሌ ከሃላፊነት በግል ምክንያት በገዛ ፈቃዱ መልቀቅ ቢፈልግ ቢያንስ ከሶስት ወር በፊት ማሳወቅ ይገባዋል።

## 8.4 የሽማግሌ ጉባኤ አባላት የስራ ድርሻ

8.4.1 የዋና ስብሳቢ (ሊቀመንበር) :- የሽማግሌ ጉባዔ ዋና ሰብሳቢ ከዚህ የሚከተሉት የሥራ ድርሻ ይኖረዋል።

1. ቤተክርስቲያን የምታካሂደውን ሥራ በሙሉ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ተጠሪነቱ ለሽማግሌዎች ጉባኤ ሆኖ ይመራል ይቆጣጠራል፣
2. የቤተክርስቲያኒቱን ጉዳይ ለሽማግሌዎች ያቀርባል።
3. የሽማግሌዎችን ጉባዔን፣ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል።
4. የቤተክርስቲያን የወጪ ደብዳቤዎች ላይ ይፈርማል።

5. መጋቢው በማይኖርበት ግዜ በሌሎች አብያተክርስቲያናት፣ በመንግስትና በማንኛውም ህዝባዊ ድርጅቶች ላይ የቤተክርስቲያን ህጋዊ ተወካይ ይሆናል።
6. ሽማግሌዎችን ለየወሩ ስብሰባ እንዲሁም ልዩ ስብሰባ በሚያስፈልግበት ወቅት ይጠራል።
7. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመደበኛው ስብሰባ ውጪ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
8. በማናቸውም በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ በሚካሄዱ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ቡድኖች ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲታየው ከቡድኑ መሪ ጋር በመመካከር ድምፅ የሌለው ሆኖ ሊገኝ ይችላል።
9. ለቤተክርስቲያኒቱን ጠቃሚ መስለው የሚታዩትን በራሱ ከመወሰኑ በፊት ወደ ለሽማግሌዎች ያቀርባል

<u>8.4.2 ምክትል ስብሳቢ:-</u> የሽማግሌዎች ጉባዔ ምክትል ስብሳቢ ከዚህ የሚከተሉት የሥራ ድርሻ ይኖረዋል።

1. ዋና ሰብሳቢውን በሚያስፈልገው በማንኛውም ጉዳይ ያግዛል፣ በሌለበትም ጊዜ ወይም በስብሳቢ በተጠየቀ ወቅት ስብሳቢውን ተክቶ አስፈላጊ የሆኑትን የቤተክርስቲያን ተግባራት ያከናውናል።
2. ዋና ሰብሳቢው በማንኛውም ምክንያት ቢያቋርጥ ተተኪ ዋና ስብሳቢ እስኪመረጥ የዋና ሰብሳቢውን ተግባራት ያከናውናል።
3. በዋና ሰብሳቢው ሲወከል ብቻ የቤተክርሰቲያኒቱን ኦፊሲል ደብዳቤዎችን ይፈርማል በተጨማሪም ቤተክርስቲያኒቱ ያዘዘችውን ተግባር ያከናውናል።

<u>8.4.3 ዋና ፀሐፊ:-</u> ዋና ፀሐፊ ከዚህ የሚከተሉት የሥራ ድርሻ ይኖረዋል።

1. ዋና ሰብሳቢውና ምክትል ሰብሳቢው በሌሉበት ጊዜ የሽማግሌዎች ጉባዔ ስብሰባ ይመራል፣
2. የጠቅላላ ጉባዔውንና የሽማግሌዎች የሥራ ስብሰባዎችን ቃለ ጉባኤ ጽፎ ይይዛል፣
3. የአባላትን ሥም ዝርዝር የያዘውን መዝገብ፣ የቤተክርስቲያኒቱን ሠነዶችና የወጪና የገቢ ደብዳቤዎች በጥንቃቄ ይይዛል እንዲያዙም ያደርጋል፣
4. እንዳስፈላጊነቱ የስራ ሪፖርት እያዘጋጀ ለሽማግሌዎች ጉባኤ ያቀርባል፣
5 . በሽማግሌ ጉባዔ የተወሰኑ ወሳኔዎችን አዘጋጅቶ በዋና ሰበሳቢ ወይም በምክትል ሰብስቢ ፊርማ ያወጣል።
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቃለ ጉባኤ የተወሰኑትን ለሚመለከተው አካል ወይም ግለሰብ በሚያመቸው መንገድ ያስታውቃል።

<u>8.4.4 ገንዙብ ያዥ/ አቃቤ ነዋይ</u>:- የመሪዎች ጉባዔ አቃቤ ነዋይ ከዚህ የሚከተሉት የሥራ ድርሻ ይኖረዋል፡

1 . በቤተክርስቲያኑ ስም የሚረከበውን ማንኛውንም ገንዙብ በሃላፊነት ይይዛል።

2. በተፈቀደው የተለያዩ በጀቶች እና መመሪያዎች መሰረት ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር ተግባራዊ ያደርጋል፡

3. የየአገልግሎቱ ወጪዎች ጥያቄ በደብዳቤ ሲቀርብለት የሰብሳቢው ፊርማ መኖሩን አረጋግጦ ተግባራዊ ያደርጋል

4. ቢያንስ በየሦስት ወሩ የቤተክርስቲያኒቱን ገንዘብ ወጪ የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርት ያቀርባል

5. በየወሩ ባለው የሽማግሌ ስብሰባ ላይ አጠቃላይ ወጪዎችን እና በባንክ ያለውን ከወጪ ቀሪ የሚያሳየውን (Bank statement) በቃል ያስታውቃል በቃለ ጉባዔም እንዲመዘገብለት ያስደርጋል።

6. የቤተክርስቲያኒቱን ገንዘብ በጠቅላላ ጉባዔ በተፈቀደው መሰረት ከዋናው ሰብሳቢ ጋር በመመካከር በሥርዓት ከፋፍሎ ይመድባል ።
7. በዓመት የአባላት ስብሰባ ላይ በኦዲተሮች የተረጋገጠ የቤተክርስቲያንዋን ጠቅላላ ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርት ያቀርባል።

8. ከዋናው ሰብሳቢው ጋር በጣምራ ፊርማ ገንዘብ ከባንክ ያወጣል።

<u>8.4.5 የሽማግሌ አባል:</u>- የሽማግሌ ጉባዔ አባል ከዚህ የሚከተሉት የሥራ ድርሻ ይኖረዋል።

1. የሽማግሌ ጉባዔ አባላት ጋር በሚያስፈልገው ሁሉ በመተባበር ይሰራል፣
2. የሽማግሌ ጉባዔን ልዩ ልዩ እቅዶችንና የውሳኔ ሃሳቦችን ተፈጻሚነት ይከታተላል

# <u>አንቀጽ 9. የአገልግሎት ስጦታዎች (የጥሪ አገልግሎት)</u>

የአገልግሎት ስጦታዎች (Ministerial gifts) ተብለው በአዲስ ኪዳን የተዘረዘሩት ዋና ዓላማቸው ቅዱሳንን ለአገልግሎት ማዘጋጀት ነው። የክርስቶስን አካል (ቤተክርስቲያን) በመገንባት ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ ትዕዛዛዊ በሆነ መንገድ የተደነገጉ ደግሞም በቋሚነት የእርሱ አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እስካለች ድረስ የተሰጡ እነዚህ ስጦታዎች በቅዱስ ቃሉ በኤፊሶን ምዕራፍ 4፡11-13 የተዘረዘሩት ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌል ሰባኪዎች፣ እረኞችና አስተማሪዎች ናቸው።

አሁን እኛ ባለንበት ሁኔታ እረኛ/ መጋቢ (Pastor) እና የወንጌል ሰባኪ /ወንጌላዊ ብቻ በአገልግሎት ተሰማርተው ስለሚገኙ ያላባቸውን ሃላፊነት እንደሚከተለው ቀርቦአል።

## <u>9.1 መጋቢ</u>

1. ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥሪ ኖሮት በቤተክርስቲያን ለማገልገል እራሱን የሰጠ ነው። ጥሪውንም በተመለከተ በሽማግሌዎች 2/3÷ 3/4÷ 4/5÷ 5/7 ኛዎቹ አምነውበት በመቀጠልም ማህበረ ምዕመናኑ ¾ ኛው የተቀበሉት ሊሆን ይገባል።
2. በወንጌል ትምህርት የሚጸና በፍቅር ፣በእምነት፣በንጽህና ፣በቃልና በኑሮ ምሳሌ የሚሆን እንዲሁም ለራሱና ለትምህርቱ የሚጠነቀቅ ሊሆን ይገባዋል።
3. መንጋውን የሚያስተምር ፣ከስህተት ትምህርት የሚጠብቅ ፣ የሚመክር ፣ የሚመግብ፣የሚያጽናና ደግሞም የሚገስፅ ሊሆን ይገባዋል።
4. ተጠሪነቱ ለሽማግሌ ጉባኤ ይሆናል።

5. አስተዳደርና ስነስርአት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በራሱ መወሰን አይችልም ፣ ሆኖም ግን የሽማግሌዎች ጉባዔ ስብሰባ እንዲጠራ ሃሳብ ያቀርባል።
6. በየሦስት ዓመታት በአገልግሎቱ ደስተኛ ሆኖ የመቀጠል ፍላጎት እና የምዕመናንም ፍላጎት ግምገማ ይካሄዳል።
7. የቤተክርስቲያኒቷን የመተዳደሪያ ደንብ የተቀበለ እና የሚያከብር ሊሆን ይገባል።

## 9.2 የመጋቢው ተግባር እና ሃላፊነት

1. ለሽማግሌዎች ጉባዔ በማስታወቅ ጉባዔውን ወክሎ ለቤተክርስቲያኒቱ ለውስጥና ለውጭ ጉዳይ ተጠሪ ነው።
2. አዳዲስ ምዕመናንን ተቀብሎ ያነጋግራል ከሌላ ቦታ የመጡትንም የመሸኛ ደብዳቤ ይቀበላል እንደዚሁም ወደሌላ ቦታ የሚሄዱትን የመሸኛ ደብዳቤ ለሽማግሌዎች ጉባዔ በማስታወቅ ይሰጣል።
3. ወደ ጌታ የመጡትን አዳዲስ ነፍሳት ስለ ድነታቸው ከተረዳ በኋላ መደበኛ የክትትል ትምህርት እንዲጀምሩ ለማድረግ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። እድገታቸውንም ይከታተላል።
4. የእሁድ የአምልኮ እና በሌላም ወቅት የሚሰብኩትን አገልጋዮችን እንደ አስፈላጊነቱ ይመድባል።
5. አብዛኛውን ጊዜ የመስበክ ሃላፊነት የመጋቢው ይሆናል።
6. በቤተክርስቲያን ውስጥ በተለያዩ አገልግሎቶች ውስጥ ያሉትን በሙሉ በአንድነት በዓመት ሁለት ጊዜ ስለ አገልግሎታቸው በእግዚአብሔር ቃል ይመክራል ደግሞም ያበረታታል።
7. ቤተክርስቲያን የወንጌል አደራዋን እንድትወጣ ወደ አላመኑቱ ሰዎች ወንጌልን ለማድረስ ከወንጌላዊ ጋር በቅርበት ይሰራል። አፈጻጸሙን ይከታተላል።
8. ምዕመናን የሚቀራረቡበት ያላቸውንም ፍቅር እንዲከፋፈሉ በአንድነትም እንዲጠነክሩ መንገድ ያዘጋጃል እንደዚሁም አባላቶችን ስለ እውነተኛ ባለ አዳራነትን በሃላፊነት ያስተምራል።
9. የጌታ ራት ሥርዓትን ይመራል።
10. የእሁድ አምልኮ ፕሮግራሞች በሰዓቱ አስጀምሮ በሰዓቱ ያስጨርሳል።
11. በእጥቢያይቱ ሽማግሌዎች በወራዊ ስብሰባ ላይ ይገኛል። እሱን በሚመለከት ነገር እና ገንዘብ ነክ ከሆኑ ጉዳች በስተቀር በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ አብሮ ይወስናል።
12. በወራዊ ስብሰባ ላይ የዕለቱን የጽሞና ጊዜ በሃላፊነት ይመራል እንዲሁም ከቃሉ የሚያካፍሉትን ይመድባል።
13. የአገልግሎት ዝርዝር ሪፖርት ለሽማግሌዎች በየሦስት ወሩ ያቀርባል ሆኖም በወር አንድ ጊዜ አጠር ያለ ሪፖርት ያሰማል።
14. የውጪ አገልጋዮችን ከሽማግሌዎች ጋር በመመካር ይጋብዛል።
15. በቤተ ክርስቲያን ሥር የሚካሄዱትን የጥምቀት፣የጋብቻ፣ሕጻናትን የመባረክ፣የቀብር ፣ የተለያዩ ሹመቶች እና የተቀሩትንም ከቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር በመተባበር ይፈጸማል።
16. መጋቢው የማስማራት ሃላፊነት ከአገልግሎቱ መካከል አንዱ ስለሆነ የምዕመናኑን መንፈሳዊ ሕይወት እየተመለከተ በልዩ ልዩ አገልግሎት ውስጥ እንዲሰማሩ ያደርጋል ይህ ሲሆን በእያንዳንዱ ምዕመናን ፈቃደኝነት ተግባራዊ ይሆናል።

17. መጋቢው ቤተክርስቲያኒቱ የምትመራበትን የዓመት ዕቅድ በማውጣት ቤተክርስቲያን የምትሄድበትን የወደፊት አቅጣጫ ከጌታ ተቀብሎ ወደ ሽማግሌዎች ጉባኤ ከዚያም ለማህበረ ምዕመናኑ በማስታወቅ ተግባራዊ ያደርገዋል።
18. መጋቢው ቤተክርስቲያኒቱ ሕጋዊ ምዝገባዋ የሚያስገድዳትን የተለያዩ ሪፖርቶችን በሽማግሌዎች ሲወከል ሥራውን ያስፈጽማል እንዲሁም በወቅቱ መከናወኑን ይከታተላል።
19. በዓመታዊ የአባላት ስብሰባ ላይ ስለ እያንዳንዱ አገልግሎት እንዲሁም ስለ ራሱም አገልግሎት አጠቃላይ ሪፖርት ያቀርባል።
20. በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል አንዲሁም የተለያዩ ሥርዓቶችን ያከናውናል።
21. መንፈሳዊ አገልግሎት ይቆጣጠራል። በሃላፊነትም ይመራል ፣ ምክር ይሰጣል በየአገልግሎት ቡድኖች ጊዜው እስከፈቀደለት ድረስ በመገኘት ያበረታታል ፣ ሆኖም ድምፅ አይሰጥም።
22. መጋቢው ምዕመናንን በማሰልጠን ደቀመዛሙርት የማድረግ ኃላፊነት አለበት::
23. መጋቢው ምዕመናንን የመጠበቅ: የመመገብ: የማጽናናትና የመጎብኘት: የመገሰጽና የምክር አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለበት::
24. መጋቢው ምዕመናንን በመንፈሳዊ ህይወታቸው በማሳደግ አገልጋዮችን የማፍራትና ቀጣይ የቤተክርስቲያን መሪዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት::

ኤፌሶን 4፡11-16፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡11-16፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡11-12፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡14፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡2-5፤ 2 ቲቶ 1፡9-11፤ ቲቶ 2፡7-8

## 9.3 ወንጌላዊ

1. ከእግዚአብሔር ጥሪ ኖሮት ጥሪውንም ከሽማግሌዎች 2/3÷ 3/4÷ 4/5÷ 5/7 ኛዎቹ አምነውበት ከቤተክርስቲያንም ምስክርነት ያለው ሊሆን ይገባል እንደዚሁም ማህበረ ምዕመናኑ 3/4 ኛውን የተቀበሉት ሊሆን ይገባል።
2. ተጠሪነቱ ለሽማግሌዎች ጉባዔ ይሆናል።
3. እራሱን ለወንጌል አገልግሎት የሰጠና ወንጌልን ለማስተማር ስጦታ ያለው ሊሆን ይገባል።
4. በአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ክትትል የሚሰራ ነው።
5. በየስፍራው እየተዘዋወረ የወንጌልን የምሥራች እያሰማ አዳዲስ ነፍሳት ወደ ቤተክርስቲያን እንዲደባለቁ የሚሰብክ ነው።
6. የቤተክርስቲያኒቷን የመተዳደሪያ ደንብ የተቀበለ እና የሚያከብር ሊሆን ይገባል።

## 9.4 የወንጌላዊ ተግባር እና ሃላፊነት

1. በወንጌል ሥራ ላይ ራዕዩን ከመጋቢው ጋር በመከፋፈልና በመመካከር እንዴት ወደ ተግባር እንደሚለወጥ ንድፈ ሀሳብ ያወጣል።
2. አመታዊ የቤተክርስቲያን የወንጌል ስርጭት አገልግሎት እቅድ ያወጣል ።
3. የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ቡድንን በበላይነት ይመራል ፤ ያደራጃል ።

4. አመታዊ የቤተክርስቲያን የወንጌል ስርጭት አገልግሎት እንቅስቃሴ ሪፖርት በመጋቢው እና በሽማግሌዎች ከታየ በኋላ ለጠቅላላ ጉባኤ ያሰማል ።
5. ከወንጌል አገልግሎት ፣ ከሌሎች አገልግሎት ክፍሎች እና ቢሮዎች ጋር በመሆን የወንጌልን ሥርጭት አገልግሎትን ያስፋፋል፤አስፈላጊ በሆነው ነገር ሁሉ መጋቢውን ያማክራል።
6. ከቤተክርስቲያን አባላት መካከል ለምስክርነት አገልግሎት የልብ ፈቃደኝነት ያላቸውን በመለየት በዓመት በተወሰኑ ወቅቶች ወደ ተለያዩ ሥፍራዎች በመውጣት መመስከር ለዚህም የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ዝግጅትን በመንደፍ ከመጋቢው ጋር በመተባበር ያዘጋጃል።
7. በጌታ ደኅንነት ያገኙትን እስከ ውሃ ጥምቀት ድረስ በማስተማር ሂደት ውስጥ ከመጋቢው ጋር በመተባበር ይሰራል።
8. መጋቢው በሚጠይቀው እና መጋቢው በማይኖርበት ጊዜ መንፈሳዊ ጥናቶችን እና ትምህርቶችን ለአጠቃላይ ጉባዔውም ይሁን ለጥቂት ቡድኖች ለማስተማር የተዘጋጀ ነው። እንዲሁም በመንፈሱ የተገለጠለት ሃሳብ ሲኖረው ከመጋቢው ጋር በመተባበር ወደ ተግባር ይለውጣል።
9. ጌታን እንደግል አዳኛቸው የተቀበሉትን ወገኖች ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና ለመጋቢው ሪፖርት ያደርጋል ።
10. በየሦስት ዓመታት በአገልግሎቱ ደስተኛ ሆኖ የመቀጠል ፍላጎት እና የምዕመናንም ፍላጎት ግምገማ ይካሄዳል።

የማቴዎስ ወንጌል 28፡19፤ የማርቆስ ወንጌል 16፡15፤ የሐዋሪያት ሥራ 8፡5፤ የሐዋሪያት ሥራ 21፡8፤ ኤፌሶን 4፡11-13

## አንቀጽ 10. የአገልግሎት ክፍሎች

የአገልግሎት ክፍሎች በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉትን አገልግሎቶች ለማከናወን በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚቋቋሙ የአገልግሎት ክፍሎች ናቸው። የአገልግሎት ክፍሎቹ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

### 10.1 የአገልግሎት ክፍል ዝርዝር

1. የእህቶች አገልግሎት

2. የወጣቶችአገልግሎት

3. የሕጻናትና የአዳጊ ልጆች አገልግሎት

4. የፀሎት አገልግሎት

5. የጋብቻ  እና የቤተሰብ ምክር አገልግሎት

6. የዲያቆናት አገልግሎት

7. የመዘምራን አገልግሎት

8. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልግሎት

9. የእርዳታና የማጽናናት አገልግሎት

10. የሚዲያ አገልግሎት

11. የወንጌል ስርጭት አገልግሎት

## 10.2 የአገልግሎቶቹ ዝርዝር ተግባር

### 10.2.1 የእህቶች አገልግሎት ክፍል

- ምድብ፦ በአንቀፅ 10 ላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው

- ተጠሪነቱ ፡ለመጋቢው ይሆናል።

የአገልግሎቱ ተግባር

1. የአገልግሎቱ ክፍል በየሁለት ወሩ የራሳቸውን ስብሰባ ያከናውናሉ በዚህን ጊዜ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እና ስለ አገልግሎታቸው ፀሎት ያደርጋሉ። በተጨማሪ ስለ አገልግሎታቸው ውይይት በማድረግ የየስብሰባችውን ቃለ ጉባዔ በጽሁፍ ይይዛሉ።

2. በቤተክርስቲያኑ ወስጥ ያሉትን እህቶች ያለባቸውን ሃላፊነት ለመወጣት የሚረዳ ትምህርት ለእህቶች ህብረት እንዲሰጥ ከመጋቢው ጋር ያመቻቻሉ። እንዲሁም እርስ በእርሳቸው የጌታን ቃል መሰረት በማድረግ በመመካከር አገልግሎቶቻቸውን ያከናውናሉ።

3. የቤተክርስቲያኒቱን ኣባሎች የሆኑትን በተጨማሪ ደግሞ ተባባሪ አባል የሆኑትንም ስማቸውንና አድራሻቸውን በመያዝ በቡድን ተያይዘው እንዲፀልዩ ያደርጋሉ።

4. ለቤተክርስቲያኒቱ ገቢ ሊያስገኝ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ እንዳስፈላጊነቱ ተሳትፎ ያደርጋሉ።

5. በቤተክርስቲያን በኩል ለሚደረግ ማናቸውም መስተንግዶ ሁኔታዎችን ያስተባብራሉ፡

6. በዓመት አንድ ጊዜ የሙሉ ቀን የመነቃቂያ ፕሮግራም በማዘጋጀት ሊያገለግሉአቸው የሚችሉትን አገልጋዮች ከመጋቢው ጋር በመመካከር ያከናውናሉ።

### 10.2.2 የወጣቶች አገልግሎት ክፍል

- ምድብ፦ በአንቀፅ አንድ(1) ላይ በተራ ቁጥር ሁለት(2) ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው

- ተጠሪነቱ ፦ ለመጋቢው ይሆናል።

<u>የአገልግሎቱ ተግባር</u>

1. የአገልግሎቱ ክፍል መሪዎች ቢያንስ በየሁለት ወሩ የራሳቸውን ስብሰባ ያከናውናሉ በዚህን ጊዜ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እና ስለ አገልግሎታቸው ፀሎት ያደርጋሉ። በተጨማሪ ስለ አገልግሎታቸው ውይይት በማድረግ የስብሰባቸውን ቃለ ጉባዔ በጽሁፍ ይይዛሉ።

2. በየወሩ ወይም በወር ሁለት ጊዜ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን የቤተክርስትያኒቱ አባሎችንና ተባባሪ የሆኑትንም በማስተባበር የራሳቸውን መንፈሳዊ ስብሰባ በቤተክርስቲያን መሰብሰቢያ ቦታ ያደርጋሉ።

3. በየሦስት ወር ወጣቶችን በማስተባበር በተለያዩ ቦታዎች የወንጌል ምስክርነትን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በመስክ ላይ ያከናውናሉ ለዚህም የሚያስፈልገውን ወጪ በተመልካች ጉባዔ በኩል ለሽማግሌ ጉባዔ በማቅረብ ያፀድቃሉ።

4. በዓመት አንድ ጊዜ በእሁድ ፕሮግራም ላይ የመዝሙርና የስብከት አገልግሎት ይሰጣሉ።

5. በዓመት አንድ ጊዜ የሙሉ ቀን ፕሮግራም ያደርጋሉ በዚህን ወቅት ያላመኑ ወጣቶችን በመጋበዝ አሳታፊ በሆነ ሁኔታ ያከናውናሉ ማለትም የመድረክ ውይይትና ስብከትና የመሳሰሉትን ነገሮች በማድረግ የሚያከናውኑ ሲሆን ወጪያቸውም በቤተክርስቲያን ይሸፈናል።

6. እንደ አስፈላጊነቱ በቤተክርስቲያን አጠቃላይ የአንድነት ጊዜ ላይ የተለያዩ ትምህርታዊና አዝናኝ የሆኑ ጉዳዮችን በስነ ፅሁፍ እና በደራማና በመሳሰሉት መንገዶች ያቀርባሉ።

## <u>10.2.3 የሕፃናትና የታዳጊ ልጆች አገልግሎት ክፍል</u>

- ምድብ፦ በአንቀፅ 10 ላይ በተራ ቁጥር ሦስት (3) ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው

- ተጠሪነቱ ፡ለመጋቢው ይሆናል።

<u>የአገልግሎቱ ተግባር</u>

1. በተወሰነው የስብሰባ ጊዜያቸው በመገኘት በህብረት መፀለይ እና አገልግሎታቸውን በተመለከተ መወያየት እና የየስብሰባቸውን ቃለ ጉባዔ መያዝና በስብሰባው ላይ የሚገኙትንና የማይገኙትን መዝግቦ መያዝ ይኖርባቸዋል።

2. በተለያዩ የዕድሜ ክልል ላይ የሚገኙትን ማለትም ከ4-12 ያሉትን በየደረጃቸው የተመደበላቸውን ትምህርት ከእግዚአብሔር ቃል ማስተማር።

3. ዕድሜአቸው ከ12 -13 ዓመት የሆናቸውን ለተመልካች ጉባዔ በማስታወቅ የድኅነት(Salvation) ትምህርት እንዲሰጣቸው ማድረግ።

4. ፈቃደኛ የሆኑትን የማያምኑ ቤተሰቦችን ልጆች ማስተማር።

5. በዓመት አንድ ጊዜ የገናን በዓል ማዘጋጀት ወጪውም በቤተክርስቲያን ይሸፈናል።

6. በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ልጆች ታንጸው እንዲያድጉ መመቻቸት ያለበትን ነገር ሁሉ ከሚመለከተው አካል ጋር እየተመካከሩ ያከናውናሉ።

7. በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ማለትም የእሁድ ሰንበት ተማሪዎች የሆኑትን ልጆች በዕድሜ ፣በፆታና በትምህርት ደረጃ መዝግበው ይይዛሉ አንድ ኮፒ ለቤተክርስቲያኒቱ ጽህፈት ቤት ይሰጣሉ በየጊዜውም ያለውን ለውጥ እንደጊዜው አስተካክለው ያቀርባሉ።

8. የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ከልጆች ጋር በተያያዘ ሥልጠና የሚወስዱበትን ሁኔታዎችን ማመቻቻሉ።

9. ከሰንበት ተማሪዎች ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ ሽርሽር (Retreat) ይሄዳሉ ወጪውም በቤተክርስቲያን ይሸፈናል።

## 10.2.4 የፀሎት አገልግሎት ክፍል

- ምድብ ፦ በአንቀፅ 10 ላይ በተራ ቁጥር አራት(4) ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው

- ተጠሪነቱ ፦ ለመጋቢው ይሆናል።

<u>የአገልግሎቱ ተግባር</u>

1. የአገልግሎቱ ክፍል መሪዎች ቢያንስ በየሁለት ወሩ የራሳቸውን ስብሰባ ያከናውናሉ በዚህን ግዜ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እና ስለ አገልግሎታቸው ፀሎት ያደርጋሉ። በተጨማሪ ስለ አገልግሎታቸው ውይይት በማድረግ የስብሰባችውን ቃለ ጉባዔ በጽሁፍ ይይዛሉ።

2. ከቤተክርስቲያን ጋር በመተባበር ምዕመናንን ሁሉ ያሳተፈ በየአቅራቢያዎቹ የአካባቢ ፀሎት ክፍል ያደራጃሉ ሁኔታውንም ይከታተላሉ።

3. በየእሁዱ ለሚደረገው አገልግሎት በየተራ የምሽግ ፀሎት እንዲደረግ የፀሉት አገልጋዮችን ይመድባሉ።

4. በየሁለት ወር ምህመኑን ሁሉ የሚያሳትፍ የጋራ ጾም ፀሎት ፕሮግራም ከቤተክርስቲያኒቱ ጋር በመተባበር ያዘጋጃሉ።

5. ከቤተክርስቲያን በሚሰጠው የፀሎት ርዕስ ላይ ምህመናኑ ሁሉ ተሳትፎ አድርገው እንዲፀልዩ ይከታተላሉ ደግሞም ያበረታታሉ።

6. በዓመት ሁለት ጊዜ በፀሎት አገልግሎት ውስጥ ላሉት አገልጋዮች የሁለት ቀን ፀሎት ወጣ ብለው የሚፀልዩበትን ሁኔታ ያደራጃሉ በዚህን ወቅት አንድ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ በውክልና አብሮአቸው በመሆን ይመራቸዋል የሚያገለግላቸው አገልጋይ ካላገኙ የተወከለው አገልጋይ ሊማሩ በፈለጉበት አቅጣጫ ትምህርት ይሰጣቸዋል። የተለየ ሃይል እንዲቀበሉም ስርአታዊ ፀሎት ዘይት ተቀብተው ይፀለይላቸዋል።

7. በዓመት ሁለት ጊዜ  በዕለተ አርብ በዓመቱ አጋማሽ እና መጨረሻ ላይ ሁሉ የሚሳተፍበት የአዳር ፀሎት በቤተክርስቲያን ያዘጋጃሉ።

## <u>10.2.5 የጋብቻ እና የቤተሰብ</u> ምክር <u>አገልግሎት ክፍል</u>

- ምድብ፡- በአንቀፅ 10 ላይ በተራ ቁጥር አምስት (5) ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው

- ተጠሪነቱ ፡ለመጋቢው ይሆናል።

<u>የአገልግሎቱ ተግባር</u>

1. የአገልግሎቱ ክፍል መሪዎች ቢያንስ በየሁለት ወሩ  የራሳቸውን ስብሰባ ያከናውናሉ በዚህን ጊዜ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እና ስለ አገልግሎታቸው ፀሎት ያደርጋሉ። በተጨማሪ ስለ አገልግሎታቸው ውይይት በማድረግ የስብሰባችውን ቃለ ጉባዔ በጽሁፍ ይይዛሉ።

2.  የመንፈቅ እና ዓመታዊ የሥራ ክንውኖቻቸዉን ሪፖርት ለመጋቢዉ ያቀርባሉ።

3. እግዚአብሔር ጋብቻን (ትዳርን) በሙሽራዉ ኢየሱስ እና በሙሽራይቱ በቤተክርስቲያን ምሳሌነት ፤ በአንድ ወንድ እና በአንዷት ሴት መካከል የሚከናወን የፍቅር ትሸር እንዲሆን መምረጡን፣ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጎ

ትምሕርት መስጠት፤ ለባለትዳሮች በዓመት አንድ ጊዜ ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር በትዳር ውስጥ ሊያውቁ የሚገባቸውን ጉዳዮች በማስተማር የሙሉ ጊዜ አንድነት ማድረግ።

4. ቅድመ፡ጋብቻ ዝግጅት፦ በዚህ ዘርፍ÷ በመጪዉ ዘመናቸዉ ጤናማ የትዳር ሕይወትን ለመምራት ለሚመኙ ወጣቶች ፤ ስለ ትዳር ሥነ፡ልቦናዊ እና መንፈሳዊ ዝግጁነት፤ አልፎም የትዳር ጓደኛ ስለ መምረጥ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት መስጠት(ሉቃስ 14÷28፡30)

5. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወላጅነት፦ ልጆችን በሚሄዱበት መንገድ የመምራት፤ ብሎም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በማሳደግ የነገዎቹ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የማፍራት፣ የአባትና እናት ኃላፊነትን፤ ወይም የክርስቲያን ወላጆችን ሚና እንዲገነዘቡ ማድረግ፤

6. በቤተክርስቲያን ውስጥ የተጫጩ ወጣቶች፣ ትጭጭታቸውን ለቤተክርስቲያን ካሳወቁ በኋላ፣ እንዴት እንደተጫጩ ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው፣ እጮኝነታቸው ተቀባይነትን ሲያገኝ፣ ወደ ትዳር ከመሄዳቸው በፊት፣ የጋበቻ ትምህርት እንዲማሩ ለቤተክርስቲያን ማሳወቅ፤ በዓመት አንድ ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ ላላገቡ ወጣቶች ጋብቻ ነክ የሆነ ትምህርት በተለያዩ መንገዶች መስጠት።

## <u>10.2.6 የዲያቆናት አገልግሎት ክፍል</u>

- ምድብ፦ በአንቀፅ 10 ላይ በተራ ቁጥር ስድስት (6) ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው

- ተጠሪነቱ፡ለሽማግሌዎች ይሆናል።

<u>የአገልግሎቱ ተግባር</u>

1. የአገልግሎቱ ክፍል መሪዎች ቢያንስ በየሁለት ወሩ የራሳቸውን ስብሰባ ያከናውናሉ በዚህን ጊዜ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እና ስለ አገልግሎታቸው ፀሎት ያደርጋሉ። በተጨማሪ ስለ አገልግሎታቸው ውይይት በማድረግ የስብሰባችውን ቃለ ጉባዔ በጽሁፍ ይይዛሉ።

2. በጋራ በሆነ የአምልኮ ጊዜ ምዕመናንን ያስተናግዳሉ መባ ይሰበስባሉ።

3. በምዕመኑ መካከል የኑሮ ችግር ያጋጠማቸው ሰዎች በቤታቸው በመሄድ ችግሩ የሚወገድበትን መፍትሔ ከቤተክርስቲያን ጋር በመመካከር ዘላቂ መፍትሔ ይፈልጋሉ።

4. በቤተክርስቲያን የማህበረ ምዕመናን የጌታ ራት ሥርአት ቀን ከመጋቢው ጋር ቀደመው በመገኘት በጋራ ይጸልያሉ በዕለቱም የሚስፈልጉትን ዕቃዎች ያቀርባሉ ለጌታ ራትና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚያልቀውንም ማንኛውንም ነገር አስቀድመው ያስታውቃሉ በጌታ ራት አገልግሎት ጊዜ በአቅራቢያ በመሆን ይከታተላሉ።

5. በህመምና በተለያዩ ሁኔታዎች በቤት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ይጎበኛሉ።

6. የጥምቀት ሥርዓት ከመደረጉ በፊት የመጠመቂያ ልብስና የጌታ ራት ያዘጋጃሉ።
7. ተጋባዥ እንግዳ ባለ ግዜ ሁሉ ማናቸውንም ነገር በመከታተል ከእህቶች እና ከሚመለከታቸው የአገልግሎት ክፍሎችም ሆነ ወገኖች ጋር በመተባበር ያስተናግዳሉ።

8. ለድቁና አገልግሎት የሚጠቀሙባቸውን ዕቃዎች በሙሉ መዝግበው ይይዛሉ እንደዚሁም ደግሞ የአገልግሎታቸውን ጊዜ(Term) ሲጨርሱ የተረከቡትን ዕቃ ለአዲሶቹ ዲያቆናት ያስረክባሉ።

9. ዲያቆናት ከተመረጡ በኋላ አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት በህዝቡ ፊት ተፀልዮላቸው አገልግሎት ይጀምራሉ።

የሐዋሪያት ሥራ 6፡1-7፤ ሮሜ 16፡1፤ 1ኛ ጤሞቴዎስ 3፡8-13፤ የሐዋሪያት ሥራ 6 ፡3

## <u>10.2.7 የመዘምራን አገልግሎት ክፍል</u>

- ምድብ፦ በአንቀፅ 10 ላይ በተራ ቁጥር ሰባት (7) ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው

- ተጠሪነቱ ፡ለመጋቢው ይሆናል።

<u>የአገልግሎቱ ተግባር</u>

1. የአገልግሎቱ ክፍል መሪዎች ቢያንስ በየሁለት ወሩ የራሳቸውን ስብሰባ ያከናውናሉ በዚህን ጊዜ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እና ስለ አገልግሎታቸው ፀሎት ያደርጋሉ። በተጨማሪ ስለ አገልግሎታቸው ውይይት በማድረግ የስብሰባችውን ቃለ ጉባዔ በጽሁፍ ይይዛሉ።

2. በሳምንት አንድ ጊዜ ከእሁድ አገልግሎት በፊት አብረው የሚፀልዩበት መዝሙር የሚያጠኑበትን ጊዜ ያመቻቻሉ።

3. ወደ ሌላ ቦታ ሄደው ለማገልገል ጥሪ ሲያጋጥማቸው በዕለቱ በአጥቢያ ቤተክርስቲያናቸው ያለው የመዝሙር አገልግሎት ክፍት እንዳይሆን አስቀድመው ለሚመለከተው ክፍል ያስታውቃሉ።

4. የሙዚቃና ሌላውንም የቤተክርስቲያን ንብረት መዝግበው ይይዛሉ ይንከባከባሉ የተረከቡትንም ንብረት ለተተኪው የአገልግሎት ክፍል ያስረክባሉ።

5. በዓመት አንድ ጊዜ የራሳቸው የሆነ የተለየ ፕሮግራም ያከናውናሉ። ወጪውም በቤተክርስቲያን የሚሸፈን ይሆናል።

6. አዳዲስ የራሳቸውን መዝሙር ከመዘመራቸው በፊት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፣ሥነ መለኮታዊ፣ሥነ ጹሁፋዊ እና ወዘተ….. የሆነው ነገር እንዲታይ የሚመለከተውን ክፍል ያነጋግራሉ ።

## 10.2.8 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልግሎት ክፍል

- ምድብ፡- በአንቀፅ 10 ላይ በተራ ቁጥር 8 ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው።

- ተጠሪነቱ ፡ለመጋቢው ይሆናል።

የአገልግሎት ክፍሉ ተግባራት

1. የአገልግሎቱ ክፍል ኮሚቴ አባላት ቢያንስ በየሁለት ወሩ ስብሰባ ያከናውናሉ። በስብሰባቸውም ወቅት ስለአገልግሎታቸውና ስለቤተክርስቲያኒቱ ይጸልያሉ፤ ስለአገልግሎታቸው ውይይት ያደርጋሉ፤ የስብሰባቸውንም ቃለ ጉባዔ በጽሑፍ ይይዛሉ።

2. ከጥሪ አገልጋዮች ጋር በመተባበር በአጥቢያ ውስጥ ያሉትን የቤተክርስቲያነቱን አባላትና እንዲሁም ተባባሪ አባላት የሆኑትን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያስተባብራሉ።

3. ከጥሪ አገልጋዮች ጋር በመሆን የአገልግሎት ክፍሉን እንቅስቃሴ በአመት ቢያንስ አንድ ጊዜ ይገመግማሉ፤ ስለአገልግሎት ክፍሉም አመታዊ ሪፖርትን በጽሑፍ ያቀባሉ።

4. ለየምድቡ የሚሰጠውን ትምህርት ቀደም ብሎ መዘጋጀት እንዳለበት ለሚመለከተው ክፍል ቢቻል በጹሁፍ ያሳውቃል።

5. ወቅታዊና ለምዕመናን መንፈሳዊ ዕድገት ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ጥናቶች እንዲዘጋጁ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ይዘት ምን መሆን እንዳለበትና ጥናቶቹ በምን ዓይነት የአቀራረብ ስልት ቢቀርቡ የተሻለ ውጤት እንደሚኖራቸው ዉይይት ያደርጋሉ:: በውይይቱም መሠረት የደረሱበትን ውሳኔ ለሚመለከተው አካል ያቀባሉ:: ከጥሪ አገልጋዮች ጋር በመሆን ቀጣይ ጥናቶች ምን መሆን እንዳለባቸው ውይይት ያካሂዳሉ።

6. ኮሚቴው ከጥናት ቡድን መሪዎች ጋር በመተባበር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ተሳትፏቸው አነስተኛ የሆኑ ምዕመናንን በመለየት ሁኔታቸውን ይገመግማሉ፤ እንደ አስፈላጊነቱም ምዕመናኑ በጥናቶቹ ተሳትፏቸው እንዲጨምር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የማበረታታት ሥራ ይሠራሉ።

7. የአገልግሎት ክፍሉ ከጥሪ አገልጋዮችና ከሌሎች የአገልግሎት ክፍሎች ጋር በመተባበር በአመት አንድ ጊዜ “የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን” በሚል ርዕስ ለምዕመናን ሁሉ የሚሆን የመነቃቂያ መረሃ ግብር ያዘጋጃሉ።

8. የአገልግሎት ክፍሉ ኮሚቴ የአገልግሎቱን አመታዊ ዕቅድና ሪፖርት ያዘጋጃሉ: በአመቱም መጨረሻ ላይ ለፓስተር ቢሮ በጊዜ ያቀርባሉ።

### 10.2.9 የሚዲያ አገልግሎት ክፍል

- ምድብ፦ በአንቀፅ 10 ላይ በተራ ቁጥር 10 ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው

- ተጠሪነቱ፡ለመጋቢው ይሆናል።

<u>የአገልግሎቱ ተግባር</u>

1. የአገልግሎቱ ክፍል መሪዎች ቢያንስ በየሁለት ወሩ  የራሳቸውን ስብሰባ ያከናውናሉ በዚህን ጊዜ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እና ስለ አገልግሎታቸው ፀሎት ያደርጋሉ። በተጨማሪ ስለ አገልግሎታቸው ውይይት በማድረግ የስብሰባቸውን ቃለ ጉባዔ በጽሁፍ ይይዛሉ።

2. በየእሁዱ ያለውን የአምልኮ ጊዜ ያለማቋረጥ  ይቀርፃሉ ::

3. በተለያዩ ጊዚያት የሚደረጉትን ማለትም የአጠቃላይ ኮንፍራንስና የማህበረ ምዕመናን ዓመታዊ  ሥብሰባ እና ልዩ የአገልጋዮች ስብሰባ ለማገልገል የሚመጡ እንግዶችን እና ቤተክርስቲያን አስፈላጊ ነው ብላ የምታምንበትን ፕሮጋራሞችን ሁሉ ይቀርፃሉ።

4. በየእሁዱ የማዕበረ ምዕመናኑ አምልኮ ላይ በጋራ ለሚዘመረው መዝሙር አመቺ እንዲሆን በየሳምንቱ ፕሮጀክተር ላይ የሚሆን ሰው ይመድባሉ።

5. በየእሁዱ ያለው የአምልኮ ፕሮግራም በቤተክርስቲያኒቱ ድህረ ገፅ እንዲተላለፍ ያደርጋሉ።

6. የተቀረፁ ትምህርቶችና ሌላም ፕሮግራሞች እየተሰሩ ለሚፈልጉ ሰዎች በሺያጭ ያቀርባሉ ገቢውም በቤተክርስቲያን አስተዳደር ለምን መዋል እንዳለበት ይወሰናል።

7. ዋና ዋና የሚባሉ መረጃዎችና ትምህርቶች በቤተክርስቲያኒቱ ድህረ ገፅ( Website) ላይ   ያስታውቃሉ።

**10.2.10** የወንጌል ስርጭት አገልግሎት **ክፍል**

- ምድብ፡- በአንቀፅ አንድ(1) ላይ በተራ ቁጥር 11 ላይ የተጠቀሰ የአገልግሎት ክፍል ነው።
- ተጠሪነቱ ፡ለመጋቢው ይሆናል።

የአገልግሎቱ ተግባር

1. የአገልግሎቱ ክፍል መሪዎች ቢያንስ በየሁለት ወሩ የራሳቸውን ስብሰባ ያከናውናሉ በዚህን ጊዜ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እና ስለ አገልግሎታቸው ፀሎት ያደርጋሉ። በተጨማሪ ስለ አገልግሎታቸው ውይይት በማድረግ የስብሰባቸውን ቃለ ጉባዔ በጽሁፍ ይይዛሉ።

2. የአመቱን የአገልግሎታቸውን እንቅስቃሴ እቅድ ያወጣሉ

3. በቤተክርስቲያን በጋራ የአምልኮ ጊዜ ላይ ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የሚቀበሉትን ሰዎች በማነጋገር ተከታታይ የድኅነት(Salvation)ትምህርት የሚሰጥበትን ጊዜ ከሰዎች ጋር ቀጠሮ ይይዛሉ ከሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ጋር በመነጋገር ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ።

4. ጌታን የሚቀበሉ ሰዎችን ሙሉ አድራሻ ይይዛሉ። ለመጋቢውም ያሳውቃሉ።

5. የታላቁ ተልዕኮ ሥልጠና በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉት አባላት ሁሉ እንዲወስዱ ከሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ጋር ያመቻቻሉ።

6. በተወሰኑ ጊዜያት በከተማና ከከተማ ውጪ የወንጌል ምስክርነት በተለያዩ መንገዶች ያከናውናሉ።

7. የመስክ አገልገሎት(Outreach Ministry) በሚያደርጉበት ወቅት ማንኛውም ወጪ በቤተክርስቲያን ይሸፈናል።

8. ለምስክርነት የሚስፈልጉ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች ከሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ጋር በመመካከር ያመቻቻሉ።

9. በአመታዊ የአባላት ስብሰባ ላይ አመታዊ የአገልግሎት እንቅስቃሴአቸው ሪፖርት በሽማግሌዎችና በፓስተር ከታየ በኋላ ለጠቅላላ ጉባዔ ያሰማሉ።

## 10.3 ዓላማ

የእነዚህ አገልግሎቶች መሪዎች በየሁለት ወሩ የሁለት ሰዓታት ስብሰባ በማድረግ በዚሁ ጊዜ ውስጥ አንዱ ሰዓት ጸሎት የሚደረግበት ሲሆን በተቀረው ጊዜ ከቃሉ በመካፈል አገልግሎትን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ የጋራ ውይይት ያደርጋሉ። የዚህ አገልግሎት ዋነኛ ዓለማው አገልግሎቶችን ሁሉ ለማጠናከር ብሎም ሃላፊነታችንን የምንወጣበትን

አቅም ጌታ እንዲሰጠንና መጠናከር የሚገባቸውን አገልግሎቶችን በማጠናከር ትስስራዊ የሆነ አገልግሎትን ለመስጠት ራእይን ሰንቆ የተመሰረተ ነው። የእያንዳንዱ የአገልግሎት መሪዎች የሚሰባሰቡበት ህብረት በመሆኑ በዚሁ ጉባዔ ላይ የሽማግሌ ጉባዔ ሰብሳቢ በቋሚነት በድምፅ አልባ የሚገኝበት የአገልግሎት ሕብረት ነው።

## 10.4 ተጠሪነታቸው

የአገልግሎት ክፍሎች ህብረት ተብለው የሚጠሩት በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉትን ጠቅላላ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ያቀፈ ሕብረት ነው። እነዚህ መንፈሳዊ ዘርፎች (Departments) በቁጥር አስራ አንድ የሆኑት በመጋቢው ቢሮ ስር የሚመሩ ናቸው፤ፀሐፊው ደግሞ ወንጌላዊው ነው።

## 10.5 አጠቃላይ መመሪያ

ከላይ የተጠቀሱት የአገልግሎት ቡድኖች አገልግሎታቸው እንደ እግዚአብሔር ቃል በትጋት ደግሞም በጋራ እንዲያገለግሉ እንዱሁም ተጨማሪ አገልጋዮችን ለማፍራት የሚያስችላቸው መመሪያ የሚከተሉት ናቸው።

1. ከላይ የተጠቀሱት የተለያዩ የአገልግሎት ቡድኖች ተጠሪነታቸው ለአገልግሎት ክፍሎች ህብረት ይሆናል ሆኖም የዲያቆናት የህንፃ ግንባታና የእርዳታና የመጽናናት አገልግሎት ቡድኖች ተጠሪነታቸው ለሽማግሌ ጉባዔ ይሆናል ሆኖም ግን የዚህ አገልግሎት አባላት ናቸው።
2. የእያንዳንዱ አገልግሎት ክፍል ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል ሆኖም የህንጻና የሚዲያ አገልግሎትን በተመለከተ እንደ አስፈሊጊነቱ እየታየ በሽማግሌ ጉባዔ ይወሰናል እንጂ እንደሌላው ኮሚቴ በየሁለት ዓመት የሚለዋወጡ አይሆንም።
3. የየኮሚቴው አባላት ቁጥር እንደ ሁኔታው የተለያየ ቁጥር ሊኖራቸው ይችላል ሆኖም ድምፅ ለመስጠት አመቺ በሆነ መንገድ ቁጥራቸው ይሰየማል።
4. የየአገልግሎቱ ክፍል ሰብሳቢዎች የአገልግሎት ክፍሎች ህብረት አባል ኮሚቴ ሆነው ያገለግላሉ
5. እያንዳንዱ አገልግሎት ክፍል/ኮሚቴ በአገልግሎታቸው የተከናወኑ ስራዎችን በየስድስት ወሩ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
6. በዓመት አንድ ጊዜ የሁሉም አገልግሎት ክፍል የሙሉ ቀን የአንድነት ጊዜ ያደርጋሉ በዚህን ጊዜ አገልግሎታቸውን በተመለከተ የትምህርት ፣የጸሎት፣የውይይት እና ቃል ኪዳን የማደስ እንዲሁም በጋር ማዕድ የመቁረስ ወቅት ሲኖር ጠቅላላው ወጪ በቤተክርስቲያን ይሸፈናል።
7. እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል የየራሳቸውን ሰብሳቢና ጸሐፊ መርጠው በወሰኑት የስብሰባ ቀን እየተገናኙ ስለአገልግሎታቸው የሚወያዩበትና የሚጸልዩበት ጊዜ እንዲኖራቸው ይገባል።

© ማሳሰቢያ

ከላይ የተዘረዘሩት መመሪያዎች ወደፊት የየአገልግሎቱ ሁኔታ እየታየ ሊሻሻሉ ደግሞም ሊለወጡም ይችላሉ።

## አንቀጽ 11. የቤተክርስቲያን ሥልጣንና ኃላፊነት

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሰረት ጌታ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን የሚከተሉትን ተግባራት እንድታከናውን ሥልጠንና ሃላፊነት እደሰጣት ታምናለች።

### 11.1 መስበክ

የክርስቶስን ወንጌል በመስበክ ሰዎች በእርሱ እንዲያምኑ ካደረገች በኋላ የቅዱስ ጥምቀት ሥርዓትን በመፈጸም አባል ታደርጋለች።

የማቴዎስ ወንጌል 28፡19-20፤ የማርቆስ ወንጌል 16፡15-16፤ የሐዋሪያት ሥራ 2፡37-42

### 11.2 ሹመት

የተለያዩ አገልጋዮችን በመምረጥ ትሾማለች።

የሐዋሪያት ሥራ 6፡1-6፤ የሐዋሪያት ሥራ 13፡1፤ የሐዋሪያት ሥራ 14፡23

### 11.3 ማግለል

አማኞችን ማስተማር ፣መምከር፣መገሰጽ፣ የማይታዘዙትን ንስሃ ገብተው ሕይወታቸውን እንዲያስተካክሉ ለመርዳትና የቤተክርስቲያንንም ምስክርነትና መንፈሳዊ ጤንነትን ለመጠበቅ እንዲሁም መንፈሳዊ ኑሮን እንደሚገባ እንዲኖሩ በሥርዓት ለመምራት እንዲያስችል በእግዚአብሔር ቃል ላይ በማመፅ ፣ ለቤተክርስትያን መሪዎችም ባለመታዘዝ የፀኑትን ከቅዱሳን ሕብረት የማግለል ስልጣን እና ሓላፊነት አላት።

የማቴዎስ ወንጌል 18፡15-18፤ የማቴዎስ ወንጌል 28፡19-20፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡1-13፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 2፡5-11፤ ገላቲያ 6፡1-2፤1ኛ ተሰሎንቄ 5፡12-15፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡2

### 11.4 ፍትህ

ከጌታ የተቀበለችውን አደራ ዓላማዋ በማድረግ በወንጌል መሪነት ለእውነትና ለፍትህ ትቆማለች።

ትንቢተ ኢሳያስ 1፡16-17፤ የሉቃስ ወንጌል 3፡19-20

### 11.5 ቸርነት

በቸርነት ሥራ አገልግሎት ትተጋለች።

የማቴዎስ ወንጌል 25፡35-40፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡9

### 11.6 ምሥጢራት

በአንቀጽ 4. ላይ የተዘረዘሩትን ቅዱሳት ምሥጢራት እና በመደረግ የሚከናወኑ ሥርዓቶችን ሁሉ ታከናውናለች።

# እንቀጽ 12. ተጨማሪ መመሪያዎች

## 12.1 የጋብቻ መመሪያ

እንደ እግዚአብሔር ቃል በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው የዘላለም ሕይወት ያገኙ ቅዱሳን በዚህ ምድር ሲኖሩ ትዳር መስርተው በመልካም ቤታቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማስተዳደር ደግሞም መምራት ይጠበቅባቸዋል። ሆኖም በትዳር ውስጥ በሚከሰቱ እንግዳ ነገሮች እንደዚሁም በውጪ በሚታዩ በጎ ባልሆኑ ተጽኖዎች በሁሉ ቦታ የጋብቻ መሰረተ ትምህርት እየተናጋ በመምጣቱ ጉዳይ ይህም በመንፈሳዊያን ሰዎች መካከል እንደ ቀላል ቸል የተባለ በመሆኑ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ቤተሰቦች ጋብቻችን ምን ዓይነት መልክ ሊኖረው እንደሚገባ ቃሉን ማዕከል ያደረገ የጋብቻ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖል።

### 12.1.1 በቤተክርስቲያን የጋብቻ ሥርዓት የሚከናወንላቸው

1. በጋራ በመፈቃቀድ ሁለቱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ መሆን ይገባቸዋል እንዲሁም ከጋብቻ በፊት በእጮኝነት በቅድስና ራሳቸውን ጠብቀው ለመጋባት መፈለጋቸውን ለቤተክርስቲያን ሲያሳውቁ የጋብቻ ሥርዓት ይፈጸምላቸዋል።

2. ጌታ ኢየሱስን ከማመናቸው በፊት የጋብቻ ውል ኖሮአቸው ጌታን ከማመናቸው በፊት በህጋዊ መንገድ ውሉን ካፈረሱ በኋላ ጌታን ቢቀበሉ እንደ አዲስ ፍጥረት ተቆጥረው ከአንድ አማኝ ጋር ጋብቻ ማድረግ ቢፈልጉ ጋብቻ ይደረግላቸዋል።

3. ጌታን ከማመናቸው በፊት በእጮኝነት ሳሉ ወሲብ አድረገው ከዚያ በኋላ ጌታን ተቀብለው ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ራሳቸውን በንፅህና ጠብቀው ለመጋባት ቢወስኑ ደግሞ ቤተክርስቲያንን ቢጠይቁ የጋብቻ ሥርዓት ይደረግላቸዋል።

4. በእጮነት ጊዜአቸው ጌታን ከማወቃቸው በፊት ልጅ ቢወልዱ በመቀጠል ሁለቱ ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድረገው ቢቀበሉ ጌታን ከተቀበሉበት ጊዜያት አንስቶ ግብረ ሥጋ ካልፈፀሙ ጋብቻ ሊደረግላቸው ይችላል።

5. ባልና ሚስት በጋራ በሚመሰርቱት ኑሮ መብትን በተመለከተ እኩል ናቸው።

## 12.1.2 በቤተክርስቲያን የጋብቻ ሥርዓት የማይከናወንላቸው

1. በሁሉ አቅጣጫ የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮት የሚቃወም ጋብቻዎችን ቤተክርስቲያን አታከናውንም ።
2. በጋብቻ ላይ ጋብቻን ማድረግ ከቃሉ ያፈነገጠ አካሄድ ስለሆነ እንደነዚህ ያሉትን ጋብቻዎች አትቀበልም ደግሞም ሥርዓትንም ኣታደርግም።
3. ከማያምን ግለሰብ ጋር ጋብቻን ለመፈጸም ጥያቄ ለሚያቀርቡ ሁሉ ቤተክርስቲያን ጋብቻውን አትቀበልም ሥርዓትንም አትፈጽምም።
4. አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ጌታን ከማግኘታቸው በፊት እንደ ባልና ሚስት አብረው ቢኖሩና ሁለቱ ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ተቀብለው የቤተክርስቲያን አባል ከሆኑ በኋላ የጋብቻ ሥነ ስርዓት እንዲደረግላቸው ቢጠይቁ እንደ አዲስ ሰዎች ሥርዓት አይደረግላቸውም ሆኖም ለጋብቻቸው እውቅና የምስክር ወረቀት ትሰጣቸዋለች።
5. አንዲት እህት ወይም አንድ ወንድም የቀድሞ ትዳራቸውን ያለ ዝሙት ምክንያት በመፍታት ከሌላ አማኝ ጋር ጋብቻን ለመመስረት ቤተክርስቲያንን ቢጠይቁ ቤተክርስቲያን የጋብቻ ሥርዓት አትፈጽምላቸውም ።
6. በጌታ የሆኑ አንድ ወንድ እና ሴት ለመጋባት ተጫጭተው ወደ ጋብቻ ሳይደርሱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢያደርጉ ቤተክርስቲያን ጋብቻቸውን አትፈጽምላቸውም። ተጋብተው ግን መኖር ይችላሉ ሆኖም እንደ ቤተክርሰቲያን አባልነታቸው ለተወሰነ ጊዜያት ከአገልግሎትና በቤተክርሰቲያን ካላቸው ሃላፊነት ለጊዜው በማሳረፍ በአመክሮ ውስጥ እንዲሆኑ ይደረጋል። ይህም የሚሆነው በተደረገው ዝሙት ሲሆን ለሌሎችም ማስተማሪያ ይሆናል።
7. አንድ አማኝ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ የእርሱ ወንድም የሚቱን ሚስት ለመውረስ ጥያቄ ቢያቀረብ ቤተክርስቲያን አትቀበልም። ሥርዓትም አይፈጸምለትም። ጋብቻውን ፈጽሞ ቢገኝ ግን ከቤተክርስቲያን አባልነት ይገለላል።
8. አንድ አማኝ በክርስቲያናዊ ጋብቻ አብረው እየኖሩ አንደኛው ወገን ወደ ዓለማዊነት ቢገባ በእምነቱ የፀናው ከቀድሞው የትዳር አጋሩ ጋር ያለው ግንኙነት የመለየት መበቱ እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡12-13 ሊሆን ይገባል።
9. በኤች አይቪ ኤድስ ምርመራ ፖዘቲቭና ኔጌቲቭ የሆኑ ሁለት ተቃራኒ ጾታዎችን ቤተክርሰቲያን አታጋባም።

## 12.2 የእጮኝነት መመሪያ

እጮኝነት በአንድ አማኝ ወንድና አንዲት አማኝ ሴት በጋራ ፈቃድ ላይ ተግባብተው አብረው በጋብቻ ለመኖር የሚስማሙበት ወቅት ነው።

1. ወደ ጋብቻ ከመሄዳቸው በፊት እጮኝነታቸውን ለቤተክርስቲያን ማስታወቅ ይኖርባቸዋል።
2. ለወላጆቻቸው ሕጋዊ በሆነ መንገድ ከማስታወቃቸው በፊት በቤተክርሰቲያን የሚሞላውን የእጮኛምነት ፎርም መሙላት አለባቸው።
3. በተለያየ አገር የሚኖሩ ከሆነ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በተመለከተ ካሉበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን የምስክርነት ደብዳቤ ማቅረብ ይገባቸዋል።

4. የእጮኝነቱ እና የጋብቻው ሁኔታ ከመፈቀዱ በፊት የኤች አይቪ ኤድስ ምርመራ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል ሆኖም ዶክመንቱ ግን በቤተክርስቲያን ውስጥ የመቀመጥ ግዴታ አይኖርም።
5. እጮኛነታቸውን ለቤክርስቲያን ከሳወቁ በኋላ ልዩ ችግር ከሌለ በስተቀር በዓመት ጊዜ ውስጥ ጋብቻቸውን እንዲፈጽሙ ቤተክርስቲያን ትመክራለች። በተጨማሪ ችግር ካለ ቤተክርስቲያን የመፍትሔ አሳብ የጌታን ቃል መሰረት ባደረገ ምክር ትሰጣቸዋለች።
6. የተጫጩ አማኞች የእጮኝነት ሕብረታቸው ሊፈርስ የሚችለው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ይሆናል፤
    - በቤተክርስቲያን ተቀባይነት ከሌለው።
    - ከሁለት አንዳቸው በሞት ቢለዩ።
    - ከሁለቱ አንደኛው እምነቱን ቢተው።
    - ከሁለቱ አንዳቸው በመናፍቅነት ትምህርት ቢያዝ እንዲመለስ ምክርን እምቢ ካለ።
    - አንዱ ወገን ቶሉ ለመጋባት ፈልጎ ሌላኛው ወገን ፈቃደኛ ባይሆን ጉዳዩ በቤተክርስቲያን ተጠንቶ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ብቻ ይሆናል።
    - በአስተምሮ ከማይመሳሰሉ ክፍሎች ጋር የሚደረግ ከሆነ ወደ ትክክለኛው እምነት ለመመጣት ፈቃደኛ ካልሆነ።
    - በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሁለቱ በአንድ ላይ መሆን ካልፈለጉ።

## <u>12.3 ከአባልነት የሚያስገልሉ በተግሳጽ የሚታዩ መመሪያዎች</u>

1. አንድ አማኝ ዘመዱን የሚያገባ ከሆነ በዘሌዋውያን 18፡6-18 በተፃፈው መሰረት ከአባልነት ይወገዳል ሆኖም ግን ድርጊቱ ትክክለኛ አለመሆኑን ሲረዳ የጀመረውን ሕብረት በንስሃ ሲተው እንደገና አባል ሊሆን ይችላል ሆኖም ወደ ተለያዩ አገልግሎቶች ለተወሰኑ ግዜያት እንዳይሳተፍ ይደረጋል።
2. የግበረ ሶዶም ልምምድ ሲፈጸም ድርጊቱ ትክክል አለመሆኑን ሲረዳ እንደገና አባል ሊሆን ይችላል። ሆኖም ለረጅም ጊዜ በምንም ዓይነት አገልግሎት ተሳታፊ አይሆንም። ይህ ውሳኔ ለሴቲቱ ግብረ ሰዶማዊትም ይሆናል። እንደገና ወደ ቀደመው ተግባራቸው ቢመለሱ ሙሉ በሙሉ ከአባልነት ይሰረዛሉ።
3. አንድ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ፣መጋቢ፣ወንጌላዊ፣አስተማሪ ፣ዲያቆን....ሆኖ የሚያገለግል አማኝ በግብረ ሰዶም ልምምድ ውስጥ ቢገኝና ቢረጋገጥበት ከቤተክርስቲያን አባልነት ይሰረዛል።
4. አንድ አባል የሌላውን ባለትዳር ባል/ሚስት ወስዶ የሚያገባ ቢሆን ከአባልነት ይወገዳል ።

……………………………………………………………………………..

# <u>አንቀጽ 13. ተደራጊ ሥርዓተ ደንቦች</u>

**13.1 ልጆችን ለጌታ መስጠት**

**13.2 የውሃ ጥምቀት**

**13. 3 የጌታ ራት**

**13.4 ጋብቻ**

**13.5 ቅብዓተ ጸሎት**

# <u>አንቀጽ 14. የሰራተኛ ደንብ</u>

<u>ማሳሰቢያ</u>

1. በ13 እና 14 ያሉት ሁለቱ አንቀጾች ማለትም ተደራጊ ሥርዓተ ደንቦች እና የሰራተኛ ደንብ ለብቻቸው በሌላ መዝገብ የሚሰሩ ናቸው።

2. መተዳደሪያው የሚጸድቀበት ጊዜው መጻፉ ልብ ይለዋል